Deanesly, Margaret, *A History of the Medieval Church 590-1500,* London, 1969.

Duckett, Eleanor Shipley, *The Gateway to the Middle Ages,* Monasticism, Ann Arbor, 1961.

Gontard, Friedrich, *The Chair of Peter,* New York,1964.

Schaff, Philip, *History of the Christian Church: Medieval Christianity,* Volume IV, 590-10-3. Hendrickson Publishers, 2002.

Zimmerman, Odo John, trans, *Saint Gregory the Great Dialogue,*1959.

# ምዕራፍ ሃያ አራት

## እውን ጴጥሮስ ቀዳሚው ጳጳስ ነውን?

ሆብስ (A. G. Hobbs) እና እኔ በመተጋገዝ የምንሰው አስን:: ይህን ስንጽፍና ስንናገር ግን ካቶሊኮች ላይ ጥላቻ ኖሮን አይደለም:: እነርሱም ክርስቶስን የቤተ ክርስቲያን ዋንኛ ያደርጋሉና፣ ሕፀፅ ግን ሰዎች ባሉበት ቦታ ሁሉ ስለሚገኝ፣ ይህ ጥንቃቄ የጎደለው አሉታዊ አስተምህሮ በእነርሱ ዘንድ ተገኝቷል::

ሐዋርያው ጳውሎስ የገላትያን ሰዎች ክርስቶስ በፊታችሁ ተስሎ ደምቆ ነበር፣ ዛሬ ግን እርሱን አትከሩራችሁ እንዳታዩ የጋረዳችሁ ምንድን ነው? (ገላ. 13) ብሎ በመጠየቅ ጥፋታቸውን እንዲያርሙ እንደ መከረ ሁሉ፣ እኔና ሆብስም የሚገባውን እንላለን::

«ግምት ይሆን ይሆናል፣ ሊነገር ስለ ኖረ፣ ያሉት ትውፊቶች ይህን ስለሚያረጋግጡ» በማለት መነሣት ፍጻሜን በግምት እና በይሆን ይሆናል ላይ ስለሚተው፣ ያንን እንደ መነሻ፣ ማጠቃለያን ደግሞ በሰነዶችና በመነሻ ምንጮች ላይ በማድረግ ምክክሩን እንጀምር::

### የመነሻ ምክክር

ይድረስ ለካቶሊኮች...



1. እውን ክርስቶስ አንድን ሰው በምድር ላይ ለምትገኝ ቤተ ክርስቲያን ራስ እንዲሆን እና እርሱም ብቸኛ ጳጳስ እንዲሆን ዐቅዶ ነበርን?
2. ክዐቀደስ፣ ለዚያ ስፍራ ያዘጋጀው ሰው ጴጥሮስ ነውን?
3. እርሱንስ የሚተኩት ተመርጠው ስፍራውን ይይዙ ዘንድ ወስኗልን?
4. እውን ጴጥሮስ የበላይነትን በተቀሩት ሐዋርያት እና በመላው ቤተ ክርስቲያን ላይ እንዲኖረው ፈቃድ ማን ሰጠው?
5. በእጁ ያለውን ሥልጣንስ ለሌሎች እንዲተላለፍ የማድረግ አቅምንና ኃይልን ተረክቧልን?
6. የጵጵስናው መንበር ሳያቋርጥ ይቀጥል ዘንድ መለኮታዊ ተፀምራትና ድንቃ ድንቆች ከጴጥሮስ ጀምሮ እየተፈጸሙ እስከ አሁን አሉን?

ከላይ በተነሡት ነጥቦች መመካከር፣ ቀናውንና ሊሆን የተገባውን ምላሽ ለመስጠት መዘገጃጀት ተከታዩን ተቀጣጣይ አሳብ አሳዳጊ ሊሆን ስለሚችል፣ አንብበን ብቻ እንለፈው::

## I. ግምት ውስጥ ከወደቁ ግምቶች እንነሣ

በሉቃስ 22:31-32 ላይ ኢየሱስ ጴጥሮስን እንደ ጸለየለት ይነግርዋል:: ከዚያም፣ «. . . እኔ ግን እምነትህ እንዳይጠፋ ስለ አንተ ጸለይሁ፣ አንተም በተመለስህ ጊዜ ወንድሞችህን አጽና [አበርታ]» አለው:: ካቶሊኮች ጴጥሮስ ጳጳስ ሆኖ ቤተ ክርስቲያንን ይመራ ዘንድ ታላቅን ኃይል በዚህ ጊዜ ሰጠው ይላሉ:: ይህን ክፍል ስናጠና ግን የምንረዳው፣ አንደኛ፣ ኢየሱስ ጴጥሮስ ደካማ መሆኑን አስቀድሞ አውቋል፤ ሊክደው እንደሚችል ተረድቷል፤ ሁለተኛ፣ ጳውሎስና ሲላስ አብያተ ክርስቲያናትን እያበረታቱ በሶሪያና በኪልቄዶን ማለፋቸውን (ሐዋ. 15:41) ሉቃስ ጽፏል፤ ጳጳሳት ግን አልነበሩም:: ሦስተኛም፣ ይኸው ክፍል ጴጥሮስን ባለማንሣቱ፣ ያህን ሰው ለቤተ ክርስቲያን መሪነት በብቸኝነት መምራቱን አልተናገረም:: ከዚህም የተነሣ፣ ካቶሊኮች

ሉቃስ 22:32ን ለጴጥሮስ ቀዳማይ ጳጳስነት ብርቱ መረጃ ሊያደርጉት አይገባም።

ዮሐንስ 21:17ን በተመለከተም፣ ኢየሱስ ጴጥሮስን «በጎቼን መግብ» ብሎታል። ይህን ካቶሊኮች እግዚአብሔር ጴጥሮስን ለቤተ ክርስቲያን ራስነት የመረጠበት መሠረታዊ ድንጋጌው ነው በማለት ይመሰክራሉ። ክፍሉን በሰፋትና በጥንቃቄ ባጠናን ጊዜ ግን ይህን መርኅ በዮሐንስ 21 ውስጥ አናገኝም። ኢየሱስ ጴጥሮስን ከሌሎች ሐዋርያት ነጥሎ መጥራቱ እርሱን ከማናቸውም በላይ አብልጦ መውደዱን አይገልጽም፤ በቁጥር 15፣ «ከእነዚህ አብልጠህ ትወደኛለህ?» የሚለው፣ «እነዚህ» ሐዋርያትን አይወክልም። ለዚህ በቂው ምክንያት፣ አንደኛ ጴጥሮስ ሌሎቹ ኢየሱስን ምን ያህል እንደሚወዱት አያውቅም፣ ሁለተኛ ጴጥሮስ ከሌሎች ሁሉ አብልጦ ኢየሱስን እንደማይወደው በገሀድ አልተናገረም፣ ምናልባት ተናግሮ ቢሆን እንኳ በመካከላቸው ወዲያው የሚፈጠረውን ውዝግብ ማየት ይችል ነበር፤ ይህ ግን አልሆነም። በስመ «በጎቼን መግብ» ትእዛዝ ጵጵስና ከመጣ፣ ጳውሎስ የኤፌሶን ሽማግሌዎችን በተመሳሳይ ሁኔታ (ሐዋ. 20:25-30) አዝዟቸው መሰናበቱን ልብ ማለት ተገቢ ነው። ይህ እንደ ዮሐንስ 21 ዋጋው እኩል ነው፤ ጳውሎስ ግን እነርሱን በቤተ ክርስቲያናት ሁሉ ላይ ጳጳሳት ይሆኑ ዘንድ አልመከረም።

እንደዚህም ቢመከር ግን፣ ካቶሊኮች ሌላ ተጨማሪ መነጋገሪያ ነጥብን ያመጣሉ፤ እርሱም ጴጥሮስን ለጳጳስነት የሚያበቃው «ቀዳሚ ተጠሪ ሆኖ መጠራቱ ነው፤ ስሙ ከሌሎቹ ሁሉ ቀድሞ መምጣቱ ሥልጣን በእጁ እንዳለ፣ ሊለየምም እንደ ተለየ ያረጋግጣል» ይላሉ። እርግጥ፣ ቀድሞ የተጠራበት ስፍራ ብዙ ነው፤ ቀድሞ መጠራት ግን ለቀዳሚነት ያበቃል ወይ? ይህን ለማብራራት፦

አንደኛ፣ ስሙ እነርሱ እንደሚሉት ሁልጊዜ ቀድሞ አያውቅም፣ ዮሐንስ 1:41 ላይ ቀዳሚ ያደረገው እንድርያስን እንጂ ጴጥሮስን አይደለም፤ ጴጥሮስንም ወደ ኢየሱስ ያመጣው እንድርያስ መሆኑን ማወቅም ተገቢ ነው።



ሁለተኛ፣ የጴጥሮስ ስም ሁልጊዜ ቀዳሚ ሆነ ማለት በብቻው ለመሪነት (ለጳጳስነት) ያበቃዋል የሚያሰኝ ማጠቃለያን አይሰጥም፣ ሰጥቶም አያውቅ።

ሦስተኛ፣ በኢየሩሳሌም ጉባኤ ዋንኛው ሰው ያዕቆብ እንጂ፣ ጴጥሮስ አልነበረም (ሐዋ. 15:14-21)።

አራተኛ፣ በገላትያ 2:9 በቀዳሚነት የተጠራውና የተጠቀሰው ሰው ያዕቆብ እንጂ፣ ጴጥሮስ አልነበረም።

አምስተኛ፣ ጴጥሮስ በአብዛኛው ክፍል ቀዳሚ ሆኖ ቢጻፍና ቢገኝ ምክንያቱ በዕድሜ በላጭነቱ፣ በባሕሪው ፈጣንነቱና ለመምራት ቀዳሚ የመሆኑ ችሎታው ሊሆን ይችላል እንጂ፣ ለቤተ ክርስቲያን መሪነት የመብቃቱ ማረጋገጫ አይደለም።

ይልቅስ፣ ጴጥሮስ የመጀመሪያው ጳጳስ እንዳይሆን የሚያበቁትን መሠረታዊ ነጥቦችን እንመልከት፦

## I. የክርስቶስ የቤተ ክርስቲያን ራስ መሆን፦

«እግዚአብሔርም ሁሉን ከእግሩ በታች አስገዛለት፣ በቤተ ክርስቲያንም፣ በማንኛው ነገር ላይ ራስ አድርጎ ሾመው እርሷም ሁሉን ነገር በሁሉም ረገድ የሚሞላው የእርሱ ሙላት የሆነች አካሉ ናት» (ኤፌ. 1:22-23)። ይኸው ትምህርት በኤፌ. 5:23 እና በቈላ. 1:18 ላይ በግልጽ ሰፍሯል። እነዚህ ክፍሎች ከ64 ዓ.ም በፊት የተጻፉ ናቸው፤ ይህም ማለት ክርስቶስ ወደ እባቱ ከተመለሰ 30 ዓመታት በኋላ ማለት ነው፤ ኢየሱስ በ33 ዓ.ም ገደማ ነበር ያረገው።

የኢየሱስ የቤተ ክርስቲያን ራስነቱ ተቋርጦ አያውቅም፤ እርሱ አይታይም፣ ግን ሁሉን ያስተዳድራል፣ ይመራል፤ ካቶሊኮች የኢየሱስ ራስነት በሰማይ ሲሆን፣ የጴጥሮስ ራስነት በምድር በምትታየው ቤተ ክርስቲያን ላይ ነው በማለት ይሞግታሉ። ጳውሎስ ለኤፌሶንና ለቈላስይስ ይህን ሲመክር፣ ጴጥሮስን የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን አልሰየመችም ነበር። እርሷ ለመሰየም የተንደረደረችው በ7ኛው ክፍለ ዘመን ላይ ነበር።

6. ጳውሎስ ከሮም ሆኖ መልእክቶችን ጽፏል፤ በጻፈው ውስጥ ግን በሮም ተጠሪ ዋንኛ ጳጳስ መኖሩን ለአንዳቸውም አልጻፈም።

## V. የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ጴጥሮስን በጳጳስነት የተቀበለችበት ምንም መረጃ የለም

1. ጴጥሮስ ከማንም በልጦ በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን አልተገመተም፤ ለዚህም መረጃው በኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን «ግዝረት + ደኅንነት» በተሰኘው የተሳሳተ ግንዛቤ መፍትሔን የሰጠው ጴጥሮስ ሳይሆን፣ ያዕቆብ ነበር (ሐዋ. 15)።
   - በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያንም ለተፈጠረው፣ ስለ ጋብቻ፣ ለጣዖት ስለ ተሠዋ ሥጋ፣ እና ስለ መላለሱት ትክክለኛ ምላሽ የተፈለገው ከጴጥሮስ አልነበረም፣ ጳውሎስ ነበር ያረመው (1ኛ ቆሮ. 7 እና 8)።
2. የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን አንድም ጊዜ ጴጥሮስን «የተከበረ አባት፣ ወይም ጳጳስ» ብላ አልጠራችውም። ይልቅስ፣ በጊዜው ኢየሱስ «እናንተ ግን፡- መምህር ተብላችሁ አትጠሩ፤ መምህራችሁ አንድ ስለሆነ እናንተም ሁላችሁ ወንድማማች ናችሁ። አባታችሁ አንዱ እርሱም የሰማዩ ነውና በምድር ላይ ማንንም አባት ብላችሁ አትጥሩ።» (ማቴ. 23፡9-10) ያላቸውን ምክር አልተዉም ነበር።
3. የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ጴጥሮስን በትልቅ ወንበር አስቀምጣ ሰዎች ሁሉ ያከብሩት ዘንድ አላደረገችም።

## VI. ሐዋርያት ሁሉ እኩል ኃላፊነትና ሥልጣን ነበራቸው

ለዚህ መረጃ፡-

1. ኢየሱስ 12ቱም ሐዋርያት በ12 ዙፋን ላይ እንደሚቀመጡ ቃል ገባላቸው፡- «እውነት እላችኋለሁ፣ እናንተስ የተከተላችሁኝ፣ በዳግመኛ ልደት በክብሩ ዙፋን በሚቀመጥበት ጊዜ፣ እናንተ ደግሞ በአሥራ ሁለቱ የእስራኤል ነገድ ስትፈርዱ፣ በአሥራ



ሁለት ዙፋን ላይ ትቀመጣላችሁ» (ማቴ. 19፡28) በማለቱ እኩል ድርሻ እንዳላቸው አሳወቀ።

ኢየሱስ ዛሬ በዙፋኑ ላይ ነው (ሉቃስ 24፡26፤ 1ኛ ጴጥ. 1፡11፤ ዕብ. 1፡3)። ከዚህም የተነሣ፣ 12ቱ ሐዋርያት ወደ እውነት ሁሉ የሚመራውን መንፈስ ቅዱስ በበዓለ ኀምሳ በተቀበሉ ወቅት በእኩል ሥልጣን ለወንጌል ሥራ ወደ ዓለም ሁሉ ተሰማርተዋል (ዮሐንስ 16፡13፤ ሐዋ. 1፡5፤ 2፡4)። በስምሪታቸውም «[ደቀ መዛሙርቱ] በየስፍራው ሁሉ ሰበኩ፣ ጌታም ከእነርሱ ጋር ይሠራ ነበር» (ማር. 16፡20) በማለት የእኩል ኃላፊነታቸውን አብስሯል።

2. በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉት ሁሉም ነበሩ፣ ጴጥሮስ በብቻው ይህን አልታደለም (ሐዋ. 2፡4)።
3. ሉቃስ በመጽሐፉ፣ «ጴጥሮስ ከአሥራ አንዱ ጋር ቆመ» (ሐዋ. 2፡14) በማለቱ፣ ሁሉም እኩል ተሰሚነት እንዳላቸው አሳውቋል።
4. ሁሉንም ሐዋርያት «ወንድሞች ሆይ፣ ምን እናድርግ?» በማለት ጠየቋቸው (ሐዋ. 2፡37)። ይህም ድርሻ እኩልነትን ያረጋግጣል።
5. በዮሐንስ 17፡14 ኢየሱስ፣ «ቃልህን ሰጥቻቸዋለሁ፤ እኔም ከዓለም እንዳይደለሁ ከዓለም አይደሉምና ዓለም ጠላቸው፣» በማለት ለሁሉም እኩል እንዳደረገላቸው አሳወቀ።
6. ለሁሉም የማስታረቅ ቃል ተሰጣቸው፤ 2ኛ ቆሮንቶስ 5፡1-19፣ «እግዚአብሔር በክርስቶስ ሆኖ ዓለሙን ከራሱ ጋር ያስታርቅ ነበርና፣ በእኛም የማስታረቅን ቃል አኖረ» በማለት፣ የሁሉም ኃላፊነት መሆኑ ታወጀ።
7. ሁሉም ሐዋርያት የክርስቶስ አምባሳደር ተደርገው ተጠሩ (2ኛ ቆሮ. 5፡20)።

ሐዋርያት እነዚህን ሁሉ መልእክቶች ሲጽፉ፣ ምንጫቸው እግዚአብሔር እንጂ፣ የሕዝቡ እስተሳሰብና ትውፊት እንዳልነበረ 1ኛ ቆሮንቶስ 2፡10-13፤ 2ኛ ጴጥሮስ 1፡21 ያረጋግጣል። ከዚህ ውጭ መንቀሳቀስ ለስሕተት ይዳርጋል።

«ወንድሞች ሆይ፣ እናንተ የተማራችሁትን ትምህርት የሚቃወሙትን፣ መለያየትንና ማሰናከያን በጉዞአችሁ የሚያደርጉትን ለዎች እንድትመለከቱ እለምናችኋለሁ፣ ከእነርሱ ዘንድ ፈቀቅ በሉ» ብሎ (ሮሜ 16:17) መምከሩን ልብ የሚል ልብ ሊለው ይገባል። የሐዋርያትን ትምህርት መቃወም ደግሞ፣ እግዚአብሔርን እንደ መቃወም ይቆጠራል (1ኛ ዮሐ. 4:6)።

## VII. አንድ ሐዋርያ በሌሎች ሐዋርያት ላይ ሥልጣን አልተሰጠውም።

ይህንን ኢየሱስ እንዲህ ሲል አስተምሯል፣ «. . . ማንም ከእናንተ ታላቅ ሊሆን የሚወድ የእናንተ አገልጋይ ይሁን፤ ከእናንተም ማንም ፊተኛ ሊሆን የሚወድ የእናንተ ባሪያ ይሁን» (ማቴ. 20:25-27) በማለት፣ አንዱ በሌላው እንዳይሠለጥን ራሱን እውነተኛ ምሳሌ በማድረግ አስተማረ።

እንግዲህ ጴጥሮስ ለጳጳስነት በብቸኝነት ከበቃ፣ ይህን ትምህርት ተጻርሯል ማለት ነው።

## *VIII. ካቶሊኮች በሐዋርያው ምትክ ሐዋርያ ያልሆነ ሰው በመተካት ተጠያቂ ሆነዋል።*

ከሐዋርያት መካከል ዕድሜ ጠግቦ የሞተው ዮሐንስ ነው፤ ይህ ሰው በ90 -100 ዓ.ም ባለው ጊዜ ነው ወደ ጌታው የሄደው፤ ጴጥሮስ ደግሞ በ64 - 68 ዓ.ም። የሚገባው በሕይወት የነበረው ዮሐንስ ነበር፣ ይህን ግን የተመለከተ ምንም እንቅስቃሴ ባለመኖሩ፣ «ለዎች ሰውን» እየተኩ እንደ ሄዱ ያመለክታል። 1ኛ ቆሮንቶስ 12:28 ስለ ጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ሲናገር፣ «እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አንዳንዶቹን፣ አስቀድሞ ሐዋርያትን፣ ሁለተኛም ነቢያትን፣ ሦስተኛም መምህራንን . . .» መደበ የሚለውን መልእክት ዘንግተዋል።



## *IX. ጴጥሮስን በመተካት ለተሰለፉት ተከታታዮች የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን መሰፈርት ያሳሟሉትን በማኖር ተጠያቂ ትሆናለች።*

ይህን በሚመለከት ከካቶሊኮች በትይዩ ሌሎች የክርስትና ቤተ እምነቶችም የሚስቱትን እናጢን፦ «ሐዋርያት» ዛሬ የሉም፣ እርግጥ ሐዋርያ ማለት «የተላከ» የሚል ፍች አለው። ኢየሱስ ራሱ በአብ የተላከ ከመሆኑ የተነሣ፣ ሐዋርያ ተብሎ ተጠርቷል፣ «የሃይማኖታችን ሐዋርያና ሊቀ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስን ተመልከቱ» (ዕብ. 3:1)፤ እንዲሁም በ2ኛ ቆሮንቶስ 8:23 የተላኩ ለሚለው የሐዋርያ አቻ ቃል አገልግሏል።

ጴጥሮስን በሚመለከት ግን አሥራ ሁለቱ ሐዋርያት፦ በኢየሱስ የተጠሩ፣ ከእርሱ የተማሩ፣ በሁሉ የዓይን ምስክር በመሆን የትንሣኤው አረጋጋጮች በመሆናቸው፣ ይሁዳን በተመለከተ ለሚደረገው ዝግጅት የተጠቀሱትን መስፈርት የሚያሟላ ተፈለገ። እንግዲህ ከዮሐንስ ሞት በኋላ ይህን የሚያሟላ ምንም ሰው አይኖርም፣ ዛሬ አለን የሚሉ ቢኖሩ፣

ሀ) የኢየሱስን ትንሣኤ በተመለከተ የዐይን ምስክር ለመሆን በይሁዳ ምትክ ምርጫ ጊዜ መለኪያ ሆነ (ሐዋ. 1:21-22)። እንዲሁም ጴጥሮስ በቆርኔሌዎስ ቤት በተገኘ ጊዜ እንዲህ አለ፣ «. . . እግዚአብሔር በሦስተኛው ቀን አስነሣው፣ ይገለጥም ዘንድ ሰጠው፤ ይኸውም ለሕዝብ ሁሉ አይደለም ነገር ግን በእግዚአብሔር አስቀድሞ የተመረጡ ምስክሮች ለሆንን ለእኛ ነው እንጂ፣ ከሙታንም ከተነሣ በኋላ ከእርሱ ጋር የበላን የጠጣን» (ሐዋ. 10:40-41) በማለት እርሱን ያዩ ለሐዋርያነት የበቁ መሆናቸውን አጸና።

ጳውሎስ በዚህ ጉዳይ ለየት ያለ ሐዋርያ ነው፤ በ1ኛ ቆሮንቶስ 15:8፣ «. . . ከሁሉም በኋላ እንደ ጭንጋፍ ለምሆን ለእኔ ደግሞ ታየኝ» በማለት፣ እርሱም በደማስቆ ጎዳና ላይ የሆነውን በማስደገፍ ከ12ቱ ጋር መቆጠሩን በማብሰር፣ ሌላ ተከታይ ማንም እንደሌለ ያረጋግጣል (ሐዋ. 22:14፤ 1ኛ ቆር. 9:1)።

3. የደፈረሰው ውኃ ይጠራ ዘንድ ውኃው በየደረጃው የሚያልፍበት የየራሱ ትላልቅ ፋብሪካ አካል ተንቀሳቃሽና የማይንቀሳቀስ የመገደቢያ ግድቦች በሰዎች ተሠርተውለታል፤ መድኃኒቶቹም በእግባቡ ተመርተው ይወጡ ዘንድ ዐይነተ-ብዙ ፋብሪካዎች በየዓለማቱ ቆመውለታል።
4. ንጹሕ ውኃ በየቤታችን የደረሰው በ«ተዐምራዊ መንገድ» አይደለም፤ በዱብ ዕዳ! ከግድቡ ተነሥቶ እየጠበበ እየጠበበ የመጣ የተዘረጋ የቧንቧ መስመር መኖሩን ልብ ማለት ተገቢ ነው-ዘርጊዎቹንና የተመረቱባቸውን ዓለማት።
5. ከ1-4 ውኃው ላይ ያተኮረ ዕልፍ «የዓለም ዓቀፍ» ሠራተኞች ተሰልፈውበታል። አሁን ደግሞ የፈላን ውኃ ሳይሆን ሻይን ሻይ የሚያሰኘው እቢሲኒያ፣ ጉመሮ፣ ውሽውሽ፣ እንበሳ ወይም ከሩቅ ዓለም የመጣውን ሻይ ቅጠል ተጠቅማችሁ ይሆናል። እነዚህ ሁሉ ከእርሻው ቦታ ተመርተው በፋብሪካው ውስጥ አልፈው ከውኃው ተገናኝተዋል፤ ግንኙነቱ ብዙ ሕዝብን አሳትፏል።
6. ሻይ ቅጠሉና ውኃው የሚገናኙበት መጠጫ ስኒ ያስፈልጋል። ስኒው ከእጃችን እንዴት እንደ ደረሰ ለመገንዘብ ታቦር ሴራሚክስ ፋብሪካን ሄዶ መጎብኘት ተገቢ ነው። እንዲትን ስኒ ለማግኘት በሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች ቀጥተኛ ተሳታፊነት አላቸው።
7. እኔ በበኩሌ ባዶ ሻይ አልወድም፤ ሁለት ማንኪያ ስኳር እፈልጋለሁ። እንኪያስ፣ ስኳር እንዴት እንዴት ተመረተ፤ ከሸንኮራ አገዳ እርሻ ምርት ጀምሮ እስከ ፋብሪካ ውጤቱ ድረስ ዕልፍ ሰው ያሳትፋል። ይህንንም ልብ ያላለ ልብ ይበለው።
8. ስኳርን ለማዋሐድ፤ እኔ «ማንኪያ» እፈልጋለሁ። ብረት-ነክ ማንኪያስ ከየት መጣ? መቼም ብረት ከምድር ሆድ በብዙ ቁፋሮ የሚገኝ ማዕድን ነው። እርሱን በፋብሪካ አቅልጦ፣ ቅርጽ አስይዞ፣ ከገበያ ገበያ አቀባብሎ ከእኛ ዘንድ መድረሱን አሁንም እናስተውል።



ሻዬ ቅመም ይኑረው፣ ወይም ትንሽ ወተት ይግባበት ካልን ደግሞ፣ በእንዲቷ ስኒ ሻይ ውስጥ በትንሹ 500,000 ሰዎች ሊሳተፉባት እንደ ቻሉ መገመት ተገቢ ነው።

ተሳታፊዎቹ የጾታ፣ የዘር፣ የቀለም፣ የዕድሜ፣ የባህል፣ የሃይማኖት ገደብ ያልከለከላቸው የሰው ልጆች ሁሉ ናቸው! ዓለሙ ሁሉ አለበት።

እንግዲህ በአንዲት ስኒ ሻይ ውስጥ ራሳችን አለንበት፣ ሌሎቹም አሉበት። ስለ «ታሪክ» በተነጋገርንና በተመካከርንም ቁጥር ይህን ማሰብ ተገቢ ነው።

ታሪክ ምንም ይሁን፣ የማንም ይሁን፣ መቼም ይፈጸም፣ ግን የትም የትም ሰዎችን ያማከለ ሆኖ ይገኛል። ኑሮዋቸው በአሉታዊም ሆነ በአዎንታዊ ገጽታቸው ቢነሣሡም፣ ሰው ሰው ሽታልና የሚጠቅም ምንነት በውስጡ አለው።

በመሠረቱ፣ የሰዎች ፈጣሪ ሕያው እግዚአብሔር ነው። እነዚህ ሁሉ ተገጣጥመው ውጤት ያለው ሥራ እንዲሠሩ የሚያደርገው እርሱ ነው። እርሱ የሁሉ ገዥና ተቆጣጣሪ መሆኑን ያሳውቅ ዘንድ፣ ሁሉንም ከአንድ ወስዶ ለሌላው ሰጠ፤ እርሱ ኖሮ ሌላውንም አኑሮ የሚዘልቅበትን ዓለም የፈጠረው ራሱ ነው፤ እናም በሰዎች ታሪክ ውስጥ ተገኝቶ ታላቅነቱን ሳያቋርጥ ያስቀጥላል።

የዓለምንም ታሪክ ለመመርመር ብንሞክር፣ የቤተ ክርስቲያንንም ታሪክ አጥርተን ለማጥናት ስንጀምር፣ ጅማሪያችን ራሳችንን የምናገኝበት ሰፍራና ሰፊው ዓለም ሳይነጣጠሉ አብረው መንጓዛቸውን ማሰብ ግድ ነው።

ስው ሆኖ ይህ ታሪክ «የእኔ ብቻ ነው፣» ያም «ገድል» የእነርሱው ነው ብሎ መጠበብ ሰፊውን የማንነታችንን መግለጫ በማጥፋት ያፋታናል፤ ተጋብተን፣ ተጣጥመን፣ ገጣጥመን ትክክለኛውን ምስል መመልከት ተገቢ ነው። ያኔ ብቻ ነው ታሪክን ተምረን፣ ተጋሪ ሆነን የምንገኘው።

እንግዲህ አንዲትን ስኒ ሻይ ከሰባተኛው ክፍለ ዘመን ዐቢይ ጉዳዮች ጋር አብረን ለማየት እንሞክር።

በመጀመሪያዎቹ 600 ዓመቶች ላይ ከዐረቢያ ምድረ በዳ እየተመመ ጦሩን ሰብቆ የወጣው «የእስላም» ጦር «አዲስን» ዓለም እንዴት እንደ ፈጠረ አብረን እንፈተሽ፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ በሞቱና በትንሣኤ ኃይል ዓለምን እያሸነፈ ያሰበት ዘመን የመጀመሪያዎቹ 600 ዓመታት እንደ ነበሩ መጻሕፍት ያብራራሉ፡፡ በእነዚህ ዓመታት ውስጥ፡-

1. ክርስትና አውሮፓን በእብዛኛው ሸፈነ፣ ሰሜን አፍሪካንና መካከለኛውን ምሥራቅ አጥለቅልቆ ክርስቲያን የሰፈነበትን ዓለም አስገኘ፡፡
2. ክርስትና የበርካታ አገሮችን ፖለቲካዊ፣ ባህላዊ፣ ማኅበራዊ፣ ግዛታዊ ልዩነቶችን ሁሉ በማቀራረብ፣ «ወጥ» የሚመስል ታላቅ መንግሥትን ወይም አንድነትን ፈጠረ፡፡
3. ክርስትና በዘላቂነት ለሁሉ መድረስ እንዲችልና፣ እርስ በርሱ የተረጋጋ ሥነ መለኮታዊ ትምህርት ይይዝ ዘንድ ጽኑ መመሪያ የሚሆኑትን መለኮታዊ ይዘት ያላቸውን 27 ቅዱሳን መጻሕፍትን ለይቶ በማውጣት አጽድቆ ተጓዘ፡፡
4. ክርስትና በሕያውነት ከተገለጠበት ዐቢይ ምልክቶች አንዱ በመሠረታዊ አስተምህሮው ላይ ዓለም አቀፋዊ ግልጽ አዋጅን በማውጣት የነገረ መለኮትን ትምህርት አቅጣጫ እንዲይዝ በተከታዮቹ ዓመታት ውስጥ ጉባኤያትን ጠርቶ ተገቢ ውሳኔዎችን አደረገ፡፡ ለምሳሌ፡-

በ325 - በኒቂያ «ክርስቶስ እግዚአብሔር ነው፡፡»

በ381 - በቁስጥንጥንያ «መንፈስ ቅዱስ መለኮት ነው፡፡»

በ431 - በኤፌሶን የሰው ልጅ ሁሉ በኃጢአት ደንካራ ነው፡፡

በ451 - በኬልቄዶን-«ክርስቶስ እግዚአብሔር ነው፣ ሰውም ነው፡፡» የሚሉ መጽሐፍ ቅዱስ-ተኮር ውሳኔዎች ተገኙ፡፡ ይህም ለዓለም በክርስትና እማካኝነት ትሩፋቶች ሁኑ፡፡ ከዚያስ፡-

1. እንዲህ ያሻቀበው ክርስትና ባሰበት በ600 ዓመት መጀመሪያ በ7ኛው ክፍል ዘመን ላይ «እስላም» በመሐመድ መሪነት ዓለምን ናጠ፡፡ ይህ መናጥ ለ600ው ዓመት መዝጊያ በመሆን ሌላን ምዕራፍ አስከፈተ፣ ያም የእስልምና መስፋፋት ነው፡፡
2. የሞኖፊስት (Monophysite) እንቅስቃሴ እና ውዝግብ ፍጻሜ በማግኘት ሌላ አቅጣጫ ተያዘ፡፡ ሞኖፊስቶች የ451ን የኬልቄዶንን (Chalcedon) ጉባኤ ያወገዙ ቡድኖች ናቸው፡፡ እነርሱ ክርስቶስን በተመለከተ የሚያምኑት «ክርስቶስ» መለኮተ-ለጡ የሆነ ማንነት ያለው እግዚአብሔር ነው የሚል ነው፡፡ በአሁኑ ጊዜ አብዛኞቹ በግብፅ፣ በኢትዮጵያ፣ በሶሪያ እና አርሜኒያ ይገኛሉ፡፡ የኬልቄዶን ጉባኤ ግን፣ «ክርስቶስ አንድ ነው፤ ግን በዘላቂነት ያልተዋሀደ ሁለት ማንነት አለው፤ ፍጹም አምላክ፣ ፍጹምም ሰው» የሚል አቋም ያላቸው ናቸው፡፡ ከዚህም የተነሣ፣ ሞኖፊስቶችና ኬልቄዶናውያን በአንዱ የባይዛንታይን መንግሥት ሥር በመሆን የሚያደርጉትን ሥነ መለኮታዊ ውዝግብ፣ እስልምና ግብፅንና ሶሪያን በማሸነፍ፣ የሞኖፊስቶችን እንቅስቃሴ በመግታት የአዲስ ምዕራፍ ጅማሮን ፈጠረ፡፡
3. የፍራንክ መንግሥት መመሥረት፡- በሻርልማኝ (Charlemagne) መሪነት የምዕራቡ ዓለም «ዘ ሆሊ ሮማን ኢምፓየር» "The Holy Roman Empire")ን ለመመሥረት አቅምን ያገኘበት የተለየ ጊዜ በመሆኑ፣ «ለአዲስ ዓለም» ጅማሮ የልዩነት መነሻ ነበር፡፡ ምሥራቁና ምዕራቡ በፖለቲካና በሃይማኖት የመለያየት አቅጣጫን የመያዝ ዝንባሌ ከ7ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ መጥቶ እንደ ነበረ ማወቅ ተገቢ ነው፡፡ ባይዛንታይን በፓትሪያርክ፣ የሮሙ በሮም ፖፕ (ጳጳስ) መተዳደር ለሁለት የተከፈለ አስተዳደርን በመፍጠር የባህል፣ የአገዛዝ፣ የግዛትም ልዩነትን በማሳደግ፣ በ1054 ዓ.ም ለፈ ስንጥቅ መፈጠሩ ለዘመኑ የቀጣይ መነሻ ሆነ፡፡

እነዚህ ሦስት ክስተቶች ክርስትና በታሪክ ውስጥ ቀድመውት ከነበሩት ክፍለ ዘመናት በተለየ መንገድ እንዲንቀሳቀስ በማስገደዱ የመካከለኛው ዘመን መነሻ ተብሎ ሊቆጠር ይችላል፡፡

በዚህ አጋጣሚ፣ የዓለም ታሪክን በክርስትና አጀንዳ ዙሪያ መከፋፈሉ የሚኖረው ድርሻ ክርስትና በአዎንታዊው ገጽታው በኅብረተሰቡ ዘንድ በጎ ተጽዕኖ የማድረግ አቅም እንደ ነበረው ያረጋግጣል::

## መሐመድ እና የእስልምና ጅማሮ

መሐመድ የሃይማኖቶችና የንግድ ማዕከል በሆነችው በመካ ከተማ ተወለደ:: መካ በደቡብ ምዕራብ በመካከለኛዋ ዐረቢያ ዳርቻ ላይ የሚገኝ ስፍራ ነው:: በዚህ ከተማ በ570-571 ዓ.ም እንደ ተወለደ ይነገራል:: በኢኮኖሚና በኃይል ብርታት ከነበረው ነገደ ኳሪሽ (Quraish) የተወለደው ይህ ሰው አባቱን ያጣው ከመወለዱ ቀድሞ ነበር! እናቱም የሞተችው በዕድሜው ስድስት ዓመት ላይ ነበር፤ ከዚህም የተነሣ፣ በአጎቱ በአቡ ታሊብ (Abu Talib) ቤት አደገ፤ አጎቱም በኢኮኖሚ እቅሙ-ደካማ በመሆኑ መሐመድ ለእነርሱ አደረ:: ይህ አገልግሎቱ ለእረኛው ጠቃሚ ነበር፤ ኋላም በዕድሜው 25ኛ ዓመት ላይ በዕድሜ ከምትበልጠው ባለጠጋ ሴት፣ ከከድጃ (Khadijah) ጋር ተጋብቶ ጡጤታማ ባደ ረገው የንግድ ዓለም ውስጥ ገባ:: በ595 ዓ.ም ካገባት ከዚህች ሴት፣ ሁለት ወንዶችንና አራት ሴቶችን አገኘ::

የመሐመድ የንግድ እንቅስቃሴ ከመካ ተነሥቶ ዐረቢያን እያቋረጠ መመለስ ስለ ነበረ፣ ከአይሁዶች እና ከክርስቲያኖች ጋር ስለ እምነታቸው ይወያይ ጀመር:: በተያያዥም፣ የዐረቦችን ነገዳዊ አምልኮን (tribal paganism) በአግባቡ አጠና::

ቁጥራቸው ትንሽ ቢሆንም፣ በኢኮኖሚ ያየሉ አይሁዶች ከመሐመድ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነትን ከንግዱ መንሥኤ የተነሣ ሲፈጥሩ፣ ክርስቲያን-ነክ ትምህርቶችን ከሚከተሉት በአገሩ ከበሩት ሞኖፊስቶች «የክርስቶስ ትስብእት በመቀላቀልና በመዋጥ ጠፍቶ የመለኮት ባሕርይ ብቻ ቀርቷል፤» ከሚሉት ጋር ተገናኘ:: ከንስጥሮሳውያንም ጋር በመገናኘት «ኢየሱስ ሁለት የተለያየ ባሕርይ ብቻ ሳይሆን፣ ሁለት የተለያየ ማንነት አለው» (Christ not only had two distinct natures, but was two distinct person.) ከሚሉት ጋር መሐመድ ደጋግሞ ተገናኘ::

በመጠን እናሳ የሆኑት ኬልቄዶናውያንም «ከተሥግዎቱ (incarnation) በኋላ አምላክነቱና ትስብእቱ ያለመቀላቀልና ያለ-መለዋወጥ፣ ያለመከፋፈልና ያለ መለያየት ይገኛል» ከሚሉት ጋር ሰፊ ንክኪ ኖረው:: በትይዩ፣ ዐረቦች ሆነው ግን ባዕዳን አምልኮን እየተዉ በአንድ ፈጣሪ የሚያምኑትም በወቅቱ ነበሩና ከእነርሱም ጋር ተዋወቀ:: ይህ ሰው ከንግዱ ገቢ በዐረፈ ቁጥር ከመካ አጠገብ ወደተገኘው ወደ ሒራ ተራራ በመሄድ ከዋሻው ውስጥ አስተንትኖትን (Meditation) ማድረግ ምርጫው አደረገ:: መሐመድ ጨዋ፣ አጥልቆ አሳቢ፣ ለእምነት የተሰጠ፣ ሀብታም ሲሆን፣ ድሆችን በመርዳት ታዋቂ ሰው ነበር:: ይህ ሰው በአረማዊ እምነት ያልረካ፣ እውነተኛ አንድ አምላክን ለማወቅ የሚጥር ሰው እንደ ነበር እስልምናን ተቃዋሚዎችና ደጋፊ የታሪክ ጸሐፊዎች መስክ ረዋል::

***

በዚህ ሰው ሕይወት 610 ዓ.ም የተለየ አቋምና ትምህርት ይዞ እንዲወጣ አደረገው፣ ያም በዓለም ታሪክ ውስጥ የአቀጣጫና የአስተሳሰብ፣ የእምነትንም የለውጥ ንቅናቄ ፈጠረ::

መሐመድ እንደሚለው፣ በዋሻው ሳለ ገብርኤል ተገልጦ የአላህ ነቢይ አድርጎ ጠራው፤ አላህ በዐረብኛ «እግዚአብሔር» ማለት ነው፤ ክስተቱ መሐመድን ስላስደነገጠው፣ ወደ ከድጃ በመሄድ፣ «ገብርኤል ይሁን ሴጣን» ያናገረኝን አላውቅም ብሎ ነገራት::

በዚህ ጊዜ ከድጃ፣ «ለቅን ሰው እግዚአብሔር መልእክተኛውን ይልክለታል እንጂ አያታልለውም» በማለት በዚያ የሚሆነውን እንዲከታተል መከረችው! ኋላም ይዞት ለመጣው እምነት ቀዳሚ ተቀባይ ሆነች! እንዲህ ለማለት የበቃችው ከድጃ ብዙዎች እንደሚስማሙበት «ባሪያህ ይስማልና ተናገር» ብሎ ኤሊ ለሳሙኤል የመከረበትን የታሪክ እውቀት በማወቋና ለክርስትና እምነት እንግዳ ባለመሆኗ ከተማረችው አንደ ነገረችው ይታወቃል::

ላይም አፍጋኒስታንና ሰሜን ሕንድ በዐረቦች ጦርነት በመሸነፍ ለእስልምና አደሩ።

ሙስሊሞች እየገፉም በሜዲትራንያን የሚገኙትን ደሴቶችም ተቆጣጠሩ። ቆጵሮስን በ648፣ በ651 ደግሞ ከትንሹ እስያ በታች ያሉትን ግዛቶች ያዙ፣ አርሜኒያንም በሰፋት ማረኩ። ኋላም ከፍተኛ ጦር በመምራት በተከታታይ ለአምስት ዓመታት (673-78) በመዋጋት ኮንስታንቲኖፕልን ለማሸነፍ ጥረት አደረጉ። ቢሆንም፣ ከ«ግሪክ እሳት» «Greek fire» የተነሣ ተጠቅተው ማሸነፍ ሳይችሉ ቀሩ። «የግሪክ እሳት» የኬሚካል ውሁድ በመሆኑ በውኃ አይጠፋም፤ ውኃ የበለጠ ኃይሉን በማደስ የጠላትን ጦር ማጥቃት የሚያስችል ተዋጊ ነው። የዘመኑ «ኒውክሌር ቦምብ» ማለት ነው፤ ኮንስታንታይን 4ኛ (668-85) ባደረገው የመረረ ጦርነትም እስላሞች ሰላምን ለመመሥረት በመስማማታቸው ወረራው ቆመ።

ወደ ምዕራብ ያደረጉት እንቅስቃሴም በ732 የፍራንክ ጦር በቻርለስ ማርቴል (መዶሻ ማለት ነጡ) ጄኔራልነት በመመራት የእስላምን የምዕራብ አቅጣጫ ጠረራን ስፔን ላይ ገታ፣ መገታቱም ለተከታታይ 700 ዓመታት ያለምንም ችግር ቀጠለ።

ሙስሊሞች ይህን ሁሉ ለማስገበር ብቃታቸው አንድነታቸው ነበር፤ ይህ ግን ብዙም ሳይቆይ ከ656 ከኦቶማን 3ኛው ከሊፋ ሞት በኋላ (Ottman the third Calliph) ክፍፍል ተፈጠረ።

አንደኛው ክፍል የጨለማውን ዓለም ሊመራ የሚገባው የመሐመድ ቤተሰብ ሲሆን፣ የአክስቱ ልጅ አሊ መስመሩን ይዞ መዝለቅ አለበት በማለት የተነሣው ሺያት አሊ (Shiat Ali) በመባል የሚጠራው ሲሆን፣ ይህ አቅጣጫ በእግዚአብሔር ከተመረጠው መሐመድ ዘር የመጣው ብቻ ሕያው ገዥያችን ይሆናል ይላሉ።

ሁለተኛው ክፍል ሱኒስ (Sunnis) ተብለው የሚጠሩት ሲሆኑ፣ መሪዎቻችንን ለማግኘት የግድ የመሐመድ ዘር መሆን የለበትም። የሕዝቡ መሪዎችና ሽማግሌዎች በነፃ ምርጫ በመምርጥ ይምሩን ይላሉ፤ እነዚህኞቹ የመረጃ ምንጫቸው ቁርአን፣ ሀዲት እና ጁማ (Qur'an, hadith, juma) ናቸው።



ይህ ክፍፍል የእርስ በርስ ጦርነትን በመካከላቸው በመፍጠር ልዩነታቸውን በመተላለቅ ገለጹ። አራተኛው አሊ መምራት ከሺያት ጀመረ፣ ግን በ661 ተገደለ፤ 5ኛው ከሊፋ ከሱኒ ሥልጣን ይዞ 661-80 ቆየ፣ ግና አንዱ በሌላው ላይ እየተነሣ የገዛ የውስጥ ችግራቸው ጉዞአቸውን ገታ።

በአሁኑ ጊዜ የሺያት እንቅስቃሴ ከሰፈነባቸው አገራት አንዷ የኢራን (የፋርስ) ግዛት ነች፤ በሰፋት ያሉት በዚህ ቢሆንም፣ በአሁኑ ጊዜ ከመላው እስላም ጋር ሲቆጠሩ እየቀነሱ በመምጣት ከ100/10 ኙ ብቻ ይይዛሉ።

በትይዩ፣ ቤተ ክርስቲያን ሙስሊሞች በሚያስተዳድሩበት አገራት ዘንድ ምን ትመስል እንደ ነበር ማወቅ ተገቢ ነው።

ሙስሊሞች በዘመኑ እስልምንና ያልተቀበሉትን የዐረብ ሕዝቦች መነሻቸው ሆኗልና ይቀበሉት በንድ ማስገደድ እንደሚያስፈልግ በማመን ከፍተኛ ጫና ፈጠሩ። ከመነሻ ግዛታቸው ውጭ ያሉትን ግን የዲፕሎማሲ መፍትሔን የመስፋፊያ ዘዴ በማድረግ መጠቀምን መረጡ። ፋርስን በያዙበት ጊዜ የቤተሰባዊውን እምነት የ(Zoroastrian) ተከታዮች አልተቃወሙም። አይሁዶችንና ክርስቲያኖችንም የአንድ አምላክ አማኞች ነን በማለት ተጽዕኖን አላመጡም፣ በሶሪያና በግብፅ ያሉትን ሞኖፊስቶችንም እስከ ገበሩአቸው ድረስ አላጠቁም። የንስጥሮስ ተከታይ የነበሩትን የፋርስ አማኞችንም አልተተናኮሉም።

በተለይ በደማስቆ የሚገኘው የቅዱስ ዮሐንስ ቤተ ክርስቲያን እስከ 750 ዓ.ም ድረስ ክርስቲያኖችና ሙስሊሞች አምልኮ ይፈጽሙበት እንደ ነበር ይታወቃል።

ይህም ቢሆን ግን፣ በሙስሊም መንግሥት ሥር የነበሩ ክርስቲያኖች ተጽዕኖ ነበረባቸው። ከተጽዕኖዎቹ ጥቂቶቹ፣ እንደ ሁለተኛ ዜጋ ይቆጠራሉ፣ በገቢ ላይ ያልተመሠረተ ግብርን ይከፍሉ ዘንድ ይደረጋሉ፣ ሠይፍና ፈረስ ሊኖራቸው አይገባም፣ በሕዝብ መካከል ሲገኙ ክርስቲያን መሆናቸው እንዲታወቅ የተለየ ልብስ እንዲለብሱ ይደረጋል፣ በሕዝብ መካከል ሲገኙ ክርስቲያን መሆናቸውን የሚያሳውቅ መስቀል ወይም የመሳሰሉ ጌጦች

አያደርጉም፣ በአምልኮአቸው ለዓት ከበሮ እና የሙዚቃ መሣሪያ አይጠቀሙም፣ ጋብቻ በክርስቲያንና በሙስሊም መካከል አይፈጸምም:: ከዚህ ሁሉ በላይ ግን፣ ወንጌልን ወደ እስላሞች ማድረስ ክልክል ነው፣ ከእስልምና ወደ ክርስትና የመጣ ሙስሊምም በሞት ይቀጣል::

እንግዲህ በእነዚህ ሁሉ የተገደቡ ክርስቲያኖች ቁጥራቸው ቀስ በቀስ እያነሰ በመሄድ መሳው ሙስሊም መሆኑ አይደንቅም:: ብዙ ስመ-ክርስቲያኖች ሙስሊም ሆነው ስመገኘት አጃቸውን የስጡት ሙሉ የዜግነት መብት ያገኙ ዘንድ በመፈለግና ከመሳቀቅ ነጻነትን ለማግኘት በመምረጥ መሆኑን ልብ ማለት ተገቢ ነው *(2000 Years of Christ Power,* p.28)::

## የክርስቲያኖች ለእስልምና ምላሽ

ሙስሊሙ ዓለም በግዛቱ ክርስቲያን ማድረግንና ወንጌልን መስበክ በመከልከሉ የወንጌል ስርጭት ተገታ:: በትይዩ ክርስቲያኖች ሊንታዘዙ የሚገባው እግዚአብሔርን ነው በማለት በጊዜው ሁለት ሙከራዎችን አደረጉ::

ጌታቸው፣ «ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ስበኩ» ባላቸው ትእዛዝ የተነሣ እስልምናን በጦርነት መቋቋም፣ እንዲሁም በጽሑፍ መዋጋትን ሥራዬ ብለው ያዙ:: ጦርነቱ እስልምናን ለመግታት፣ እንዲሁም የተያዙ ይዞታዎችን በማስለቀቅ፣ የኃይል ሚዛንንም ተጠሪ በማድረግ ክርስትናን ለማስፋፋት የተሻለ አማራጭ ሲሆን፤ በትይዩም፣ የእስልምና ድርሳናትን ከመጽሐፍ ቅዱስ አኳያ በመመርመር የተቃውሞ ጽሑፎችን በመጻፍ የመቋቋም ጥረት ፍሬያማነትን አምጥቷል::

ትምህርት ላይ በጊዜው የነበሩ የዐቃቤ እምነት ጸሐፊዎች:- ሀ) በመሐመድ፣ ለ) በእስተምህሮተ እግዚአብሔር ላይ ለፊ ሥራ ሠርተዋል፤ በጊዜው በመጽሐፈ ራእይ በተጻፈለት ሐሰተኛ ነቢይ አርሉ መሆኑን በማሳወቅ፣ በትይዩም ሙስሊሞች በዮሐንስ 14:16 «ሌላው አጽናኝ» የተባለለት ዐውዳዊ ፍቺ መሐመድን ሳይሆን፣ መንፈስ ቅዱስ መሆኑን አስተማሩ::



አስተምህሮ ሥላሴን በተመለከተም፣ እስልምና፣ ይሁዲነት፣ እና ክርስትና የአንድ አምላክ አማንያን የሚለው የጋራ ግንዛቤን አስመልክቶ፣ እስልምና ክርስትናን እንደ ብዙ አምላክ አምላኪ የቆጠረበትን በማረም፣ እንዲሁም የኢየሱስን አምላክነትና ሰውነት በመግለጥ በውስን የተሻለ የነገረ መለኮት ደረጃ ላይ ተደረሰ::

# ምዕራፍ ሃያ ስድስት

## ሊዮ እና 717

በክፍተቱ መካከል የሚገኙት ዓመታት ለባይዛንታይን መንግሥት የጦርነት ዘመኖች ነበሩ:: የምሥራቁ የሮማ መንግሥት በድግግም ከሦስት የተለያዩ አቅጣጫዎች ጦርነቶች ነበሩበት::

አንደኛው፣ ከሙስሊም ዐረቦች እና በመካከለኛው ምሥራቅ ከሚገኙት ቱርኮች ጋር::

ሁለተኛው፣ በባልካን ከሚገኙ አረማውያን ነገዶች እና ከስሜኑ ሕዝብ ጋር::

ሦስተኛው፣ በምዕራብ ካሉ «ክርስቲያን መንግሥታት» ጋር ጦርነቶች ነበሩበት:: ባይዛንታውያን በመጠቃት ግዛታቸውን ሲያጠብቡ፣ በማሸነፍ ግዛታቸውን ሲያስጠብቁ የነበረበት ወቅት ያህ የዘመን ክልል ነው::

ጥቃቶች ቢኖሩም፣ ባይዛንታይን በሥነ ጥበብ፣ በሥነ ጽሑፍ፣ በነገረ መለኮት፣ በመንፈሳዊ ሕይወት ምንነት ላይ ለዓለም ገጸ በረከትነቷ አልተቋረጠም ነበር::

ሊዮ የኢዙሪያን (Leo the Isauran, 717-41) ተወለደባት የተባለችው በትንሿ እስያ የምትገኘውን የስፍራ ስም መለያው አድርጎ መንግሥቱን በባይዛንታይን ሲጀምር፣ መሠረታዊ ለውጥም በምሥራቅ ቤተ ክርስቲያን እንደ ጀመረ ታሪክ ይዘክራል::

ሊዮ የመንግሥት ሥልጣን ይዞ ሥራ ሲጀምር የምሥራቅ ቤተ ክርስቲያን በምስል እና በሥዕል የምትፈጽመው አምልኮ ስሕተት በመሆኑ፣ የክርስቶስ ነው ብለው ከቀረጹት ምስል ጀምሮ

ዘመቻውን አጧጧፈ፣ በበርካታ ገዳማት ያሉትን መነኮሳት በማስወጣት የጦሩ የመስፈሪያ ጣቢያ አደረጋቸው።

ምስል አፍቃሪ-የነበረውን «ቅዱስ» እስጢፋኖስ ዘ አወዘንተስንም ንጉሡ (Stephen of Saint Auxentus) በ767 አስገደለው። ይህን ከማድረጉ በፊት ግን እስጢፋኖስ ተስሚና ተወዳጅ ሰው በመሆኑ፣ ወደ አንዲት ደሴት በግዞተኝነት እንዲዛወር አደረገው፣ በኋላም መልሶ ወደ ቆንስታንቲኖፕል በማስመጣት አሳሰረጡ። በዚህ ወቅት ምስል-አፍቃሪ የሆነው ሕዝብ እስር ቤቱን ከበበ፣ እስጢፋኖስም በእስር ቤት ውስጥ ቤተ ክርስቲያንን አቋቁሞ አምልኮተ-እግዚአብሔርን ጀመረ። ከዚህ በኋላ ነበር ኮንስታንታይን ይህ ሰው እንዲገደል ያዘዘው። ወታደሮችም «የመንግሥቱ ተቃዋሚ ይሄ ነው በድንጋይ ውገሩት» በማለት በወገራ ተገደለ።

ምስል-አፍቃሪያን ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እስጢፋኖስ አዲሱ ሰማዕት በማለት ጠሩት። በ754 ኮንስታንታይንም 338 ጳጳሳትን በመጥራት ቆንስታንቲኖፕል ላይ ጉባኤ አደረገ። ይህ ጥሪ ምስል-ጠሎችን ያማከለ እንጂ፣ ምስል-አፍቃሪ ከነበሩት ከአንጾኪያ፣ ከአሌክሳንድርያ፣ ከኢየሩሳሌምና ከሮም ያሉ ጳጳሳትን አላካተተም። በውሳኔውም፣ «ምስል ለቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊነት የሚያግዘው ምንም ነገር የለም፣ ጠዖተ አምልኮን ያስፋፋል እንጂ» በሚል ተደመደመ።

በምስል አፍቃሪዎች ላይ ያለ ስደትና ግድያ ረገብ ያለው በኮንስታንታይን ልጅ በሊዮ 4ኛ (Leo IV, 775-80) ጊዜ ነበር። የዚህ ሰው ሚስት ለምስል የወገነች ስለ ነበረ፣ ባለቤቷ ስደቱን እንዲገታ አግባባች፣ ሆነላትም። ባለቤቷ ከሞተ በኋላ ደግሞ፣ ለንግሥና ባልደረሰው በልጇ በኮንስታንታይን 6ኛ ቦታ (Constantine VI, 780-97 ዓ.ም) በመንገሥ የቀደሙት መሪዎች የሄዱበትን ጎዳና ተቃራኒውን ተራመደች፣ በ787ም ታላቅ ጉባኤን በኒቂያ ጠራች። ይህ ጉባኤ ከ325 በኋላ የተደረገ የኒቂያ ድጋሚ ስለ ነበረ፣ ሁለተኛው የኒቂያ ጉባኤ ተብሎ ይጠራል።

ጉባኤውም ምሥራቃውያንና ምዕራባውያንን የጠቀለለ በመሆኑ፣ «ሁሉን አቀፍ ጉባኤ» በመባል ይጠራል። በዚህ ጉባኤ የተወሰነው



ምስል አፍቃሪዎች እንዳይሰደዱና ተቃውሞ እንዳይደርስባቸው የሚል ነበር። ኋላ ግን በ802 ሞግዚተ መንግሥት የነበረችው ኢሬኒ (Irene) ከተገለበጠች በኋላ ነገሮች ሁሉ ወደ የሊዮ የመነሻ ውሳኔ ተመለሱ። ከዚያም በኋላ በመንግሥቱም በተከታታይ ሥልጣን ላይ የወጡት ምስል-ሰባሪ (ጠል) ሆነው በመገኘታቸው፣ ብዙዎችን ጨረሱ፣ ብዙዎችም ተሰደዱም።

በምስል ላይ የተነሣው ልዩነት ግን ለመጨረሻ ጊዜ የተጠቃለለው በቴዎዶራ (Theodora) የሥልጣን ዘመን ሆነ። ይህቺ ንግሥት ስለ ልጇ ሚካኤል ሣልሳዊ (Michaei III) ሞግዚት በመሆን ሥልጣን ያዘች። ሴቲቱ በ843 ጉባኤን በመጥራት በኒቂያ በ787 ተወስኖ የነበረውን የምስል-አፍቃሪ ውሳኔን ተግባራዊ እንዲሆን አደረገች። ይህም በምሥራቅ ቤተ ክርስቲያናት ዘንድ «የኦርቶዶክሶች ድል» "The Triumph of Orthodoxy" በመባል ተጠራ። ከዚህን ጊዜ ጀምሮ ምስልን በመጠቀም ማምለክ የማይከለክል የምሥራቅ ቤተ ክርስቲያናት መለያ በመሆን፣ ኦርቶዶክሶች በይፋ «ምስሎች ሰማይንና ምድርን የሚያገናኙ ድልድዮች» ናቸው በማለት በይፋ ይጠሯቸው እና ያምኑባቸው ጀመር።

በምስል ላይ ተቃውሞ በሊዮ ከተጀመረበት ጊዜ ጀምሮ በመንግሥትና በቤተ ክርስቲያን መካከል ግጭቶች ኖሩ። ይህ ይፈጠር ዘንድ ካደረጉት ምክንያቶች አንዱ፣ «የቤተ ክርስቲያን የበላይ መንግሥት ሊሆን ይገባዋል» የሚል ፖለቲካዊ አጀንዳ ሲሆን፣ ይህም በየጊዜው የነገሡት ነገሥታት ፍላጎት እንደ ነበር ከታሪክ ማረጋገጥ ይቻላል። ይህን ማለት ከሚያስችሉ ምክንያቶች አንዱ፣ በርካታ የምሥራቁ መንግሥት መሪዎች ምስሎችን ቢቃወሙም፣ በየራሳቸው ስም የተሠሩትን የገዛ ምስሎችና ቅርጾችን ግን መከበሪያቸው በማድረግ በየአደባባዩ አቁመው ነበር።

***

ለምን ይሆን ብዙ ጦርነት የተደረገበት የተቃውሞ እንቅስቃሴ በ843 በተደረገው ውሳኔ እልባት በማግኘት የምሥራቅ ቤተ ክርስቲያን በምስል አፍቃሪነት የጸናችው? ይህን መመለስ

ምስል-አፍቃሪዎች ግን ይህን ይቃወሙታል! «ኢየሱስ እኮ ፍጹም የሰው ልጅ ነው። ከዚህም የተነሣ፣ ሰው መሆኑን ማወቅ የምንችለውና የምንገነዘበው በምስል ሰውነቱን በአግባቡ መግለጽ ስንችል ነው። እርግጥ ነው፣ ቅድመ-ሰውነቱ በፊት ያለውን ይዘታ መግለጽ አይቻልም! የኋላ ማንነቱን ግን ምስል ይገልጠዋል፤ ኢየሱስ ሰው በመሆን አካል ደምና ሥጋ አለው። ይህን መሸፋፈን ግን ኢየሱስን በሰውነቱ እንዳናውቀው ማድረግ ነው። ይህም ለሰው ልጆች የመጣበትን መሠረታዊ ምክንያት ያጠፋል! በማለት ምስል-ጠሎችን ይገደዳራሉ።

## ገለጻ ሦስት

የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን በዚህ ጉዳይ ላይ የነበራት ልምምድ ምን ነበር? የዚህ ጥያቄ ምላሽ መሠረታዊ ነው። ከዚህም የተነሣ፣ ምስል-ጠሎች በተለይ እስከ አራተኛው ክፍል ዘመን ድረስ «ምስል-ሥዕል» ምንም ዐይነት አገልግሎት እንዳልሰጠ በማረጋገጥ፣ እነርሱ ያልተቀበሉትን መጠቀም ውሉታ-ቢስነት ነው በማለት አፍቃሪዎቹን ይኮንናሉ።

በእውነትም የቤተ ክርስቲያን አባቶች ምስልን አልተጠቀሙም። ይልቅስ፣ ምስል-ተኮር እንቅስቃሴ ከ4ኛው ክፍለ ዘመን በኋላ «ለቤተ ክርስቲያን እንደ መጣላት የተቆጠረው ነጻነት» ይዞት ወይም አካትቶት ያስገኘው ውጤት ነው። ይህ ደግሞ በተለይም ወንጌልን ለማድረስ ጎርጎሪዎስ በተንቀሳቀሰበት መንገድ ላይ የአረማውያንን ቤተ መቅደሶች በመቀደስ ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ያውል ነበር። ይህ አነሣስ ምስሎችንም በተመለከተ ራስነታቸውን ወደ መንፈሳዊ ምንነት አሳድገውታል። ይህንንም ኋላ ላይ የተረዱ ሁሉ ሊዮ የወሰደውን ዐይነት እቋም በመውሰድ ማረም ተገቢ ነው በማለት ይሞግታሉ።

በተያያዥ፣ ምሥራቆች ክርስቶስን ሰው አድርገው ምስል ሊያበጁ፣ ምዕራቦች ግን ክርስቶስን በበግ በመመስል ይጠቀሙ እንደ ነበር ማወቅም በዚህ የታሪክ ገለጻ ላይ አዳባሪ ነጥብን ያስነሣል። ምሥራቆች ምዕራቦችን ኢየሱስን ከሰውነት ወደ እንስሳነት በማምጣት የአረማውያን ጣዖታት ያመልኩ የነበረበትን



ፈለግ በመከተል ያሳስታሉ በማለት ይወቅሷቸዋል። የመነሻ ነጥቡን በተመለከተ በቤተ ክርስቲያን አባቶች ዘንድ ምንም ሰነድ በመጥፋቱ፣ ምስል-አፍቃሪዎች ሌላ ድጋፍን «ከትውፊት» ለማግኘት ጥረት ያደርጋሉ። ይህም-የቂሣሪያው <u>ዩሴቢየስ</u> (Eusebius of Caesarea) በወቅቱ የታሪክ ቀማሪ ስለ ነበረ፣ በዘገባው ውስጥ «የሐዋርያው ጳውሎስ፣ የጴጥሮስ እና የክርስቶስ የገጽታ ባለ ቀለም ሥዕል ተሥሎ እንደ ነበረ ይታወቃል» በማለት ጽፏል። ከዚህም በመነሣት፣ ሥዕል-አፍቃሪያን ነበሩ በማለት ይወዛገባሉ።

ዩሲብየስ ግን በእቋም ምስልን መጠቀም ለመንፈሳዊነት ምንም እስተዋጽኦ የለውም በማለት ይቃወም እንደ ነበረ ተጽፎለታል።

## ገለጻ አራት

ማንበብ ለማይችሉ አማንያን ዕድል ፈንታቸው ምን ይሆን? የሚል ጥያቄን ምስል-አፍቃሪዎች በማንሣት ይወዛገባሉ። ምስል-ጠሎች «ይህ ጣዖትን በማስመለክ ሕዝብን ማጥፋት ነው! እልተማሩምና በትንሹ መነሻ የሆነችው «ክርስቲያን-ተኮር» የመሰሉ ምስሎች የበለጠ እነርሱን ወደ ማምለክ ስለሚያድግ፣ ሕያው ከሆነው ከማይታየው እግዚአብሔር ጋር አይገናኙም» በማለት ይፋለማሉ።

ምስል-አፍቃሪዎቹ ግን፣ «ምስሎች ሁሉ መጻሕፍት ሆነው ያገለግላሉ፣ ክርስቶስን፣ ሐዋርያትን፣ የቤተ ክርስቲያን አባቶችን፣ ሰማዕታትን በማየት ብዙ ቁም ነገሮችን ሊገነዘቡ ይችላሉ። እነዚህ አማንያን ማንበብ እቃታቸው እንጂ፣ ማስተዋል አልተከለከሉም» በማለት አቋማቸውን ያሳድጋሉ።

የደማስቆው ዮሐንስም ይህን በተመለከተ፣ «ጽሑፍ ለሚያነብቡ፣ ምስሎች ፊደል ላልቆጠሩ ወሳኞች ናቸው» ይላል። በተጨማሪም፣ ምስል-አፍቃሪዎች፣ «በቋንቋ ተጠቅመን ባነበብንና በተናገርን ቁጥር የደረጀ ምስል በኅሊናችን ይፈጠራል! ምስልንም ስንመለከት ኅሊናችን ያነብባቸዋል። ከዚህም የተነሣ፣ ምስል-ጠሎች ያለ ምስል ኖረውም አያውቁ» በማለት ሙግታቸውን ያሳድጋሉ።

መንግሥቱ እድንቆ አይሸልመውም፣ በሞቱም ሰማዕት በማሰት እያከብረውም ነበር::

የምዕራብ መንግሥትና የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ግን በመስቀል ጦርነቶች ተፋልሞ «ላሰፈ» ስሙን በሰማዕትነት መዝግባ ታከብረዋለች፣ ለእግዚአብሔር መንግሥት የበቃ በማድረግም ትቆጥረዋለች:: ይህን እቅጣጫም በመያዝ የመጀመሪያው የመስቀል ጦርነት በ1096 ዓ.ም በምዕራብ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን አጋፋሪነት ተጀመረ::

## 2. የጦርነቱ መሠረታዊ መንሥኤ

መንሥኤው የታላቁ ባይዛንታይን ንጉሠ ነገሥት አሌክስዩዝ ቀዳማዊ (Alexius I Comnenus, 1081-1118) በቱርክ ሙስሊሞች በመወረር የግዛቱን ክፊል ተነጠቀ፤ በባልካን የትንሿ እስያ ክልል በመሸነፍ ተዋረደ:: በዚህ ጊዜ የምዕራቡን ጳጳስ ኧርበን ዳግማዊን (Urban II, 108-99) ይረዳው ዘንድ ጠየቀ:: ጥያቄው ጦር በመላክ ኃይሉን ያጠናክርለት ዘንድ ነበር:: ይህ ጥያቄ ከመድረሱ በፊት ግን፣ የምዕራቡ ክፍል የአውሮፓን «ክርስቲያን» በማስተባበር ወደ ኢየሩሳሌም ለመጓዝ ቅድመ-ዝግጅት ላይ ነበር:: የሚጓዙት የተቀደሰችውን ምድር ለማየት፣ የጌታን መቃብር ለመመልከት፣ ቅዱሳን ሐዋርያት የረገጡትን፣ የሄዱበትን በመነካካት መንፈሳዊ በረከትን ለማግኘት በመፈለግ ነበር::

የእግዚአብሔር ልጅ የቀደሰውን ስፍራ ማየት፣ ደሙ የፈሰሰበትን ስፍራ ደርሶ መመልከት በምዕራብ ክርስቲያኖች ዘንድ ልዩ ስፍራን እንደሚያስገኝ ያምኑም ነበርና ነው ተደራጅተው የተነሡት:: የምሥራቁ ቤተ ክርስቲያን ግን፣ ኢየሩሳሌምን በተመለከትም ሆነ በሌሎች በቅዱሳን ንብረትና ማንነት ላይ የምዕራባውያንን ያህል ቁብ የላቸውም::

ከ1055 ዓ.ም ጀምሮ ግን ቱርኮች ኢየሩሳሌምን ሙሉ ለሙሉ ተቆጣጥረው ስለ ነበር፣ እነዚህ ሙስሊሞች በቅንነት፣ በፍቅር ወደዚያ የመጡ ተጓዦችን ያስተናግዷቸው ነበር:: ከዚህም የተነሣ፣ ወደ «ተቀደሰችው ምድር» ለመምጣት አይፈሩም:: በኋላ ላይ ግን የቱርክ ሙስሊሞች ወደ ኢየሩሳሌም



በሚጓዙት የምዕራብ ካቶሊክ ክርስቲያኖች ላይ ግፍ መፈጸም ጀመሩ:: በገዞ ላይ ግብር መጫንን፣ መብት ገፈፋንና ግድያን ይፈጽሙባቸው ጀመር::

ይህ ምግባራቸው በምዕራብ ክርስቲያኖች ዘንድና በቱርክ ሙስሊሞች መካከል መካረርን በመፍጠር ግጭቱ ናረ:: በዚህ ወቅት ነበር ጳጳስ ዳግማዊ ኧርበን (Urban II) የባይዛንታይንን የእርዳታ ጥያቄ ለመመለስ ከፍተኛ ቅድመ-ዝግጅትን ያደረገው:: በተለይም በኅዳር 1095 ዓ.ም ታላቅ ጉባኤን ጠራ:: ልዑላን፣ መኳንንት፣ የቤተ ክርስቲያናት መሪዎችን በክሌርሞንት (Clermont, Southern France) ጠራ:: ጉባኤው ውይይቱን አስፍቶ በዘጠነኛው ቀን ላይ የኧርበን የመዝጊያ ቃለ ስብከት ለጉባኤው ቀረበ::

ቃለ መልእክቱ «የምዕራብ አውሮፓ ንጉሦች፣ ልዑላን በተለይም በፈረንሳይ ያሉ አለቆች መጋጨትን ከዛሬ ጀምሮ አቁሙ፣» የሚል ትእዛዝ ነበረበት:: ይህም የተቀደሰችውን ምድር በእጃቸው እስኪያስገቡ ድረስ የሚከበር መሆኑን አስረዳ፣ ተሰብሳቢው በስሜት ውስጥ ሆኖ «ይህ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው!» እያለ ለመዝመትና ለማዝመት በአንድ ኃይል ተነሣ:: ይህ ለመጀመሪያው የመስቀል ጦርነት የመነሻ መሠረት ሆነ:: በዚህ ወቅት የተደረገው የምዕራብ ክርስቲያኖች መነሣሣት በቀጥታ ሃይማኖታዊ እንቅስቃሴ ሲሆን፣ ሁሉም በአንድነት «የኢየሱስን የመቃብር ስፍራ ነፃ ማውጣት» አሉብን የሚል መነሻን ይዘውበታል፤ በትይዩም ግዛትን ለማስፋፋት የፈለጉ ፊውዳሎችና ድሆች ሀብትን ፍለጋ ተቀላቅለው ነበር::

ዳግማዊ ኧርበን (Urban II) በስብከቱ:- ማርቆስ 8:34ን መሠረት አድርጎ ሲሰብክ፣ «ሊከተለኝ የሚወድ ሁሉ ራሱን ይካድ፣ የገዛ መስቀሉንም ይዞ ይከተለኝ» የሚለውን ክፍል መሠረት አድርጎ፣ «የገዛ መስቀሉ» የሚለው ቃል የሚፈጸመው ለዚህ ጦርነት በመዝመትና የእግዚአብሔርን መንግሥት በመሥዋዕትነት በመውረስ ነው::» የሚል ፍቺ ተሰጠው:: ከዚህም የተነሣ፣ በተለይም የመስቀል አርማን መሠረት በማድረግ መውጣት ዋንኛ መለያ ሆኖ አገለገለ:: በተለይም በ3ኛው የመስቀል ጦርነት

ከየአገራቱ ለጦርነት በወጡት የባንዲራቸው መልክና የመስቀል ይዞታ የተለያየ ሆኖ ኅብርን እንደ ፈጠረ ይነገራል። እንግሊዞች ነጭ መስቀልን፣ ፈረንሳዮች ቀይ መስቀልን፣ ፍሌምሾች (Flemish) አረንጓዴ መስቀልን ይዘው ወጡ።

በእነዚህ ጦርነቶች ሊታወስ የሚገባው ዐቢይ ነጥብ ሥርዓተ ፊውዳሊዝም በተንሰራፋበት ዘመን ጦርነቱ እንዲቀሰቀስ በመደረጉና አዝማቾቹ ፊውዳሎች መሆናቸው፣ የግዛት መስፋፋትን ጐን ለጐን የማስኬድ ዓላማ እንደ ነበራቸው በድጋሚ ልብ ማለት ተገቢ ነው።

እነዚህ ተዋጊ ፊውዳሎች እንደ መሪ ወደ ቤተ ክርስቲያን በመምጣት ሰይፋቸውን ስለ ቤተ ክርስቲያን፣ ስለ ሴቶቻቸው፣ ስለ ድሀ አደጎች፣ ስለ ድሆችና፣ ስለ ወንጌል አገልጋዮች በማለት ይባረክ ዘንድ ወደ ባራኪው ያመጡ ነበር። በዚህ ሁሉ ለጦርነቱ የዘመቱ የካህናትንና የሊቀ ካህናትን ያህል ተከበሩ፣ ለእግዚአብሔር እንደሚዋጉ ስለ ተነገራቸው በዚህ አመኑ።

አባ ጎት የተባለ ሰሜን ምሥራቅ ፈረንሳይ (1053/65-1125) የኖረ ሰው በጻፈው ሰነድ ላይ የወቅቱን የዘመቻ ግፊት ሲያስነብብ፡-

> «በእኛ ዘመን እግዚአብሔር ራሱ ጦርነት አዘጋጀ፤ ለዚህም ጦርነት የተንቀሳቀሱ ሁሉ በአዲሱ ጎዳና ላይ በመዝለቅ ደኅንነትን ያገኙ ዘንድ ተፈቀደ፣ ዘማቾች ዓለምን ንቀው ለመሥዋዕትነት ገስግሰዋል። ከእነርሱ የሚፈለግ ሌላ ተጨማሪ ነገር ምንም የለም» በማለት ነበር።

ሁለተኛው የመስቀል ጦርነትም ሲጀመር ጳጳስ ኢጉኒየስ ሣልሳዊ (Pope Eagenius III, 45-53) ለዘማቾች በእርግጠኝነት የነገራቸው፣ «ቱርኮችን በመዋጋት የተቀደሰችውን ምድር ነፃ ለማውጣት የተነሣችሁ ሁሉ የዘላለም ሕይወት ለእናንተ ሆናላችኋል፣» የሚል ነበር።

በዚህ ሁሉ ግን የምዕራባውያን ባህል የአባትን ሀብት ሙሉ ለሙሉ የበኩር ልጅ ይወርስ ዘንድ የሚፈቅድ በመሆኑ፣ ተከታይ ልጆች በሙሉ መናጢ የመሆን ዕድል ነበራቸው። ይህ ጦርነት በታን በማስገኘት ትልቅ ድርሻ ስለ ነበረው፣ ወደ መካከለኛው ምሥራቅ መሄድ ዋና አጀንዳ መሆኑን ልብ ማለት ተገቢ ነው።



## 3. ታሪክ ቀዳማይ የመስቀል ጦርነቶች (1096-99)

በዳግማዊ ኧርባን የጦርነት ጥሪ ከመደረጉ በፊት በርካታ ሕዝባዊ የመስቀል ጦርነቶች ተካሂደዋል፣ በተለይም የፈረንሳይ መነኩሴ የነበረው ጴጥሮስ (Peter, 1050-1115) «ራእይ ተሰጠኝ» በማለት ስብከተ መስቀላዊ ጦርነትን በድግግም አደረገ፣ በሰበከም ቁጥር ሰዎች ስለ ኃጢአታቸው ያለቅሱ፣ ጠሳቶቻቸውን ይቅር ይሉ፣ የፈረሰ ትዳራቸውን ያድሱ፣ ገንዘባቸውን ለቤተ ክርስቲያን ይለግሱ ነበር። ከዚህም የተነሣ፣ ቱርኮች ያደረጉትን ግፍ እየዘከረ 200,000 ያህል የአርሶ አደር ዘማቾችን ለበሰበ።

እነዚህ የተሰበሰበ ወራሪዎችም በእስልምና ላይ ድል እንደሚያደርጉ በማመን ወደ ፓለስቲና በደቡብ ጀርመን አድርገው ገሠገሡ፣ በመንገዳቸውም ያገኙዋቸውን አይሁዶች ጨረሱ፣ ይህም ዐረ-ሴማዊ አቋም እንደ ነበራቸው አመላከተ፣ ዘልቀው ወደ ትንሹ እስያ በደረሱ ጊዜ ግን ቱርኮች ጨፈጨፏቸው፤ በሠለጠኑ የቱርክ ወታደሮችና በአርሶ አደር ጀብደኞች በተደረገ ውጊያ የማሸነፍ ድርሻው ለቱርክ ሙስሊሞች ሆነ።

ጴጥሮስ (Peter) እስተባበረው ግን በ1099 ኢየሩሳሌም ከቱርኮች ነፃ በወጣች ጊዜ ከጭፍጨፋው በማምለጥ መገኘቱ ሁሉን ያስገረመ እንደ ነበረ ጸሐፊያን ይተርካሉ።

በትይዩ ግን፣ በኮንስታንቲኖፕል ከረምቱን ሲደራጅ የከረመ 300,000 ሺህ የሠለጠነ ወታደር የባይዛንታይን መንግሥት ባመቻቸው መሠረት ወደ ጦርነቱ ዘለቀ። በወቅቱ የቱርኩ መንግሥት እርስ በርሱ በመጋጨት እየተከፋፈለ ያለበት ወቅት ስለ ነበረ፣ ጦርን አስከትቶ የደረሰውን የቱርክ ሠራዊት ድል እየነሳ ገሠገሠ። በዚህም ጉዞው በ1097 ኒቂያን፣ በ1098 አንጾኪያን፣ በ1099 ኢየሩሳሌምን ከቱርኮች በማስለቀቅ አሸነፈ።

ጉዞው ረሀብ፣ ወረርሽኝ፣ እና ተደጋጋሚ ጦርነት የበዛበት ስለ ነበር፣ ኢየሩሳሌም ሲደርስ የቀረው የጦር መጠን 20,000 ብቻ ነበር። እነዚህኞቹ ያለ ምንም ርኅራኄ ያገኙትን የቱርክ ሙስሊሞችንና አይሁዶችን ገደሉ፣ ለሴቶችና ለልጆች አልራሩም

ነበር:: ይህ የመጀመሪያው የመስቀል ጦርነት በውጤቱ በቱርክ የተወሰዱትን በምዕራብ የሚገኙትን የትንሿን እስያ አገራትን አስለቅቆ ለባይዛንታይን መንግሥት መመለስ ዐቢይ ተግባሩ ነበር::

ይህም ምሥራቅ ክምዕራቡ ጋር በመተጋገዝ የመጣ ሆነ:: ድል በተነሣበት ሰፍራ ግን የሮም መሪዎች አራት መንግሥታትን መሠረቱ፤ ያንንም በኢደሳ (Edessa)፣ በአንጾኪያ (Antioch)፣ በትሪፖሊ (Tripolis)፣ እና በኢየሩሳሌም (Jerusalem) በማቆም «የላቲን መንግሥታት» ተገዥ መሆናቸውን አወጁ:: የጦሩ መሪ የነበረውም ጎድፍሬይ (Godfrey) በኢየሩሳሌም ንጉሥ ተብሎ ተሰየመ:: ተሿሚው ግን «ክርስቶስ በነገሠበት ከተማ ዘውድ አልጭንም፣ ክርስቶስ የሾክ አክሊል በጫነበት እኔ ወርቅ አላደርግም፣ «የመቃብሩ ጠባቂ» ወይም <The Defender of the Holy Tomb> ተብዬ እጠራለሁ» በማለት ለራሱ ስምን ሰጠ::

ጎድፍሬይ እስከ 1100 ዓ.ም ድረስ ገዝቶ ሲሞት፣ ወንድሙ ቦልድዊን (Balldwin) ስፍራውን ይዞ በኢየሩሳሌም ንጉሥ ሆኖ ተጠራ:: በዚህም ሥልጣን እስከ 1118 ዓ.ም በመግዛት ቂሣርያን በ1101 ዓ.ም፣ ቤይሩትን በ1110 ዓ.ም ያዘ::

የላቲን ተናጋሪ ቤተ ክርስቲያን የሆኑት የምዕራብ ካቶሊክ ጦር መሪዎችም ባሸነፉ ቁጥር የምሥራቅ ቤተ ክርስቲያናትን በማስገበር የራሳቸውን ላቲን ተናጋሪ ጳጳሳትንም መሾም በመጀመራቸውና የምሥራቅ ምእመናንን ማጎሳቆልና ማዋረድ በመያዛቸው፣ ቅራኔ በመካከላቸው አደገ::

## ታሪክ ሁለተኛው የመስቀል ጦርነት (1147-49)

በላቲን መንግሥት ተዳዳሪ የነበረችው የኢዴሳ (Edessa) መንግሥት ዳግመኛ በቱርክ ወታደሮች በ1144 ዓ.ም መያዝ ይህን ሁለተኛውን የመስቀል ጦርነት ከፈተ::

ለመስፋፋቱ ሁኔታን ያመቻቸው በርናርድ (Bernard,1090-1153) በመባል የሚጠራው ሰው ነበር:: ይህ ሰው በእናቱ እቅፍ በማደግ ፍቅሯን እየተመገበ ባለበት ዕድሜው ሞተችበት:: በዚህም ኀዘን



የቆየው ሰው በ22 ዓመቱ በ1112 ዓ.ም መመንኮስን የሕይወቱ ምርጫ አድርጎ ተነሣ፣ በዚህም ስለ ክርስቶስ ራሱን በማስገዛት መኖሩን ጀመረ:: በርናርድ መሳጭ ሰባኪ ከመሆኑ የተነሣ ብዙዎች በስሙ አይጠሩትም፣ «ማር አፍላቂው መምህር» ይሉት ነበር:: የስብከቶቹ ማዕከል «እግዚአብሔር ፍቅሩን በክርስቶስ ገልጦታል፣ እኛም በተራችን እርሱን መውደዳችንን ሰዎችን በመውደድ እንገልጽ» የሚል ነበር::

ማርቲን ሉተር ኋላ ላይ ስለዚህ ሰው ሲናገር፣ «በርናርድ በስብከቶቹ ሁሉ የሚወዳደረው በላጭ አልተገኘም፣ ቅዱስ አውግስጢንም አልደረሰበትም፤ ለዚህም ምክንያቱ ክርስቶስን አግዝፎ መግለጡ ብቻ ነው» በማለት መስክሯል::

ሌላው የበርናርድ ትምህርት መገለጫ የዘላለምን ምንነት በሚገልጽበት ሰዓት ሰማይን ወደ ምድር በማቅረብ የምድር ሰዎች ወደ እግዚአብሔር ይናፍቁ ዘንድ ማድረግ መቻሉ ነበር:: ይህ አቅሙ በዘመኑ በርካቶች እናቶች ልጆቻቸውን ደብቀው፣ ሚስቶችም ባሎቻቸውን ወደ እርሱ ሰበካ እንዳይሄዱ ተጠንቀቀው ይቆጣጠሩ እንደ ነበረ ተጽፎለታል::

በርናርድ ክርስቶስን በወደደው መጠን ለማርያምም ስፍራ ያለው ሰው መሆኑ አስገራሚው ገጽታው ነበር:: ማርያም በበርናርድ ገለጻ፣ «የሰማይ በር፣ የውብት ድንበር፣ የሰው ልጆች ባለ ውለታ» ነች:: እንደ እርሱ አባባል፣ «ክርስቶስ መካከለኛ በመሆን በሰው ልጅ እና በእግዚአብሔር መካከል ሲገኝ፣ ማርያም ደግሞ ከክርስቶስ ጋር ሆና ማማለዷን አታቋርጥም» ይላል:: በተጨማሪ፣ «እግዚአብሔር በቁጣው ቢመጣባችሁ፣ ወደ ኢየሱስ ሽሹ፣ ወደ ኢየሱስ መሄድ ብትፈሩ፣ ወደ ማርያም ገስግሱ» በማለት ይሰብክላት እንደ ነበር ይታወቃል::

በርናርድ በሰባኪነቱ፣ በጸሐፊነቱ እና የገዳማት መሥራች በመሆኑ ብዙ ሰዎች እርሱን ያውቁታል፣ ይፈልጉታል፣ ያደምጡታል:: በ1130 ዓ.ም ካርዲናሎች ተሰብስበው ሁለት ጳጳሳትን ለምርጫ አቅርበው ነበር፣ ዳግማዊ ኢኖሰንት (Inocent II) እና ዳግማዊ አናክትየስን (Anacteus)፣ በርናርድ ኢኖሰንትን ደግፎ

የሚገለጹበት አነጋገር፣ «የእኔ ካህን ክርስቶስ ነው፣ የእርሱም መሥዋዕትነት ለእኔ ነው» የሚል ነበር።

- ዋልዴንሳውያን በዘመናቸው ሁሉ ቅዱሳን መጻሕፍትን እንዲያስረክቡ ተጠይቀው እምቢ ብለዋል፣ በዚህ እምቢ ባይነታቸው ዋጋ ከፍለዋል። «ራሳቸውን እንደ አቤል፣ የሮማ ካቶሊክንም እንደ ቃየል ቆጥረው ኖረዋል፤» እንኪያስ እነዚህ. . .

ሀ. ዋልዴንሳውያን እነማን ናቸው?

ለ. መነሻቸው የት፣ መድረሻቸውስ ምን ነበር?

ሐ. ከእነርሱስ ምን መማር ይቻላል?

በሮም ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሆኖ ለ20 ተከታታይ ዓመታት የሚያደርጉትን ሁሉ በመኮነን ይሰብክ የነበረው ስሙ-ጥር ፒየሪ ብሩየስ (Pierre Brueys) ይባላል። ይህ ሰው በ1126 ዓ.ም በቅዱስ ጊለስ በራፍ ላይ እንዲቃጠል ተደርጓል።

ፒየሪ፣ «ሕፃናትን አናጥምቅ፣ መጠመቅ የተገባቸው ሰዎች አጥምቁን ይበሉ፤ ያማሩ ሕንፃዎችን ማነጽ ይብቃ፤ እውነተኛ አምልኮተ እግዚአብሔር ለቃሉ መገዛት ብቻ ነው፣» በማለት መስበኩ ለሞት አብቅቶታል።

የሮም ካቶሊክን እንደ ተቋም ያስቆጣት ዋና ነጥብ ግን በቅዱስ ቁርባን ስም የምንወስደው ኅብስትና ወይን፣ ኅብስቱም ኅብስት፣ ወይኑም ወይን እንጂ የክርስቶስ ሥጋና ደም አይደለም ማለቱና መታሰቢያነቱን ብቻ ማወጁ የሞቱ ቀዳሚ ምክንያት ሆኗል።

የእርሱ ዘመነኛ ሆኖ ፈለጉን የተከተለው የኩሉኒው ሄነሪ (Henri of Cluny) ነበር። ይህ በኩሉኒ በድቁና ያገለግል የነበረው ሰው፣ እግዚአብሔር ሰጠኝ በሚለው የንግግር ችሎታው፣ የተቀናበረ ቃለ ሐቲት በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ በመመሥረት መስበኩን ተያያዘ። ብዙ ካህናት ተቃወሙት፣ ተገዳደሩት፤ ተግዳሮታቸው ግን በሚሰጠው ፈጣን ምላሽና አጣብቂኝ ንግግሩ ሊቋቋሙት አልቻሉም።

ታዋቂ የነበረው የክሌርቮው በርናርድ (Bernard of Clairvaux) ግን ክርስቶስን እያገነነ ማርያምንም በማክበሩና የአገናኝነት አቅም



በመስጠቱ፣ የዘመኑ የሮማ ካቶሊክ መሪዎች በርናርድን ተከትለው ሄነሪን ማሳደድ ጀመሩ። በእንክርት ላይ እያለም ተይዞ ታሰረ፤ ብዙዎች እንደሚሉት፣ በመከራ ብዛት በእስራት ላይ ሳለ ሞቷል፣ ወይም በቱሉዝ (Toulouse) በ1147 ዓም አካባቢ ተገድሏል።

እንደ ፒየሪ እና ሄነሪ የመሰሉ እንቅስቃሴዎች ከእነርሱም በፊት እንደ ነበሩ የሚታወቅ ሲሆን፣ ይህን መሰል «ከመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ ጋር እንጣጣም» የሚለው አካሄድ በስፋት የመጣው ግን ለዋልዴንሳውያን የስያሜ ምክንያት የሆነው የፒተር ዋልዶ (Peter Waldo) በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ መገኘት ነበር። የዚህ ሰው የልደት ዓመቱ በውል ባይታወቅም፣ ወደ ክርስቶስ የሄደው ግን በ1217 ዓ.ም ነበር።

ፒተር የሊዮን (Lyons) ከተማ ነዋሪ እና ነጋዴም ነበር፣ በአገሩ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ውስጥ ትልቁን ቦታ ይዞ የሚንቀሳቀስ የዘመኑ ከበርቴ ነበር። ፒተር ባዘጋጀው ታላቅ ግብዣ ላይ ወዳጁ በድንገት ይሞታል፣ በዚህ ሰው ሞት ራሱን መመዘን፣ ለመንፈሳዊ ሕይወት ምንነት መዘጋጀት፣ መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ መደበኛ ሥራው አድርጎ ተንቀሳቀሰ። ከቅዱሳን መጻሕፍት የተነሣ፣ ስለ ዘላለም ሕይወት እና ክርስቲያን ስለ መሆን መሠረታዊ እምነትን በማግኘት «በክርስቶስ ዳንኩኝ» የሚል ምላሽን በአደባባይ በመስበክና በማስተማር ጀመረ።

በተለይም በ1160 ዓ.ም አዋቂ ጸሐፊና ተርጓሚ በመቅጠር እርሱና ሕዝቡ ሊረዳው በሚችል ቋንቋ መጽሐፍ ቅዱስን በከፊል ማስተርጎሙ ቃሉን ለመረዳት ያለውን ጉጉት ከዳር አደረሰለት። አንድ ወቅትም ላይ የቅዱስ አሌክስየስን (St. Alexius) ግለ ታሪክ ሊያነብ ያስተዋለው ገለጻ ሕይወቱን በጌታ አቅጣጫ መራለት።

አሌክስየስ በቂ ሀብት ነበረው፤ ሀብቱን፣ ንብረቱን ሁሉ ሸጠ፣ ከዚያም ወደ «ተቀደሰችው ምድር» ወደ ኢየሩሳሌም በመናኝነት ዘመተ። ይህ ድርጊቱ በፒተር ሕይወት ውስጥ ስፍራን ስላገኘ፣ ማቴዎስ 19:21ን በሕይወቱ ይመዝነው ዘንድ ወሰነ፤ «ኢየሱስም፦ ፍጹም ልትሆን ብትወድ፣ ሂድና ያለህን ሸጠህ ለድሆች ስጥ፣ መዝገብም በሰማያት ታገኛለህ፣ መጥተህም ተከተለኝ፣» አለው

የሚለውን መመሪያ ፒተርም ወድዶ ተቀበለው። የሀብቱን ውስን ድርሻ ለሚስቱ ትቶ የተቀረውን በሙሉ ሸጦ ለድሆች አከፋፈለ፣ ይህንንም በ1173 ዓ.ም አደረገው።

እስከ 1180 ዓ.ም ፒተር መጽሐፍ ቅዱስን ለማንበብ ጊዜውን ሁሉ ሰጠ፣ ከዚያም ከጌታዬ የተቀበልኩት መልእክት አለኝ፣ ወንጌልን እየዞርኩ እሰብካለሁ፣ በዙረቴም ሁሉ ጌታ እንዳለው፣ «ሁለት ሁለት አድርጎ በየቦታው ላካቸው፣ ደቀ መዛሙርቱ መከሩ ብዙ ነው ሠራተኛው ግን ጥቂት ነው፣ ከዚህም የተነሣ የመከሩን ጌታ ሠራተኞች እንዲልክ ጸልዩ፤ በተኩላዎች መካከልም እልካችኋለሁ፣ በጉዞአችሁ ተጨማሪ ሸንጣ፣ ልብስና ጫማ ሳትያዙ ወደ የታዘዛችሁበት ሂዱ» ያላቸውን መሪ ቃል፣ ፒተር ይህ ለእኔ ነው በማለት አምኖ ተነሣ። ይህንንም የአገሪውን የቤተ ክርስቲያን መሪ ጠየቀ።

ለጠየቀው የተሰጠው ምላሽ ግን እርሱና ቢጤዎቹ ሁሉ ከፈረንሳይ ታዋቂ ከተማ ከሊዮን (Lyons) ተጠራርገው ይወጡና ይንከራተቱ ዘንድ ከማድረግ ባሻገር፣ በ1184 ዓ.ም በመናፍቅነት ተፈርጀው ይሰደዱ፣ ይገደሉ ዘንድ ትእዛዝ ወጣ። በመነሻቸው ላይ የሊዮን ድሆች (The poor men of Lyon) በመባል ይጠሩ የነበሩት፣ ኋላ ላይ ከስብከታቸውና ከመስጠታቸው በተጨማሪ ክርስቶስን ብቻ አጉልተው ለሚሰብኩና ለሚከተሉ ሁሉ ስያሜያቸው መለያቸው እየሆነ፣ «የመንፈስ ድሆች» መሆናቸውን ገለጹ።

በዘመናቸው ከላሻቸው የነበረው ዴቪድ የኦግስበርጉ (David of Augsburg) «የሊዮን ድሆች» በውጫዊ ገጽታቸው ትሑት፣ ሰው አክባሪ፣ እሺ ባይ እና ክርስቶስ-መሰል ሕይወትን የሚኖሩ ይመስላሉ፣ ውስጣቸው ግን በትዕቢት የተነፉ የዲያብሎስ ልጆች ናቸውና ተጠንቀቁ» *(The Pligrim Church, p.115)* በማለት ሸሙጡን ጻፈ።

እነዚህን መሰል ተቃውሞዎች ከፒተር ጋር ያሉትን በአብዛኛው ወደ ጀርመን ዘልቀው በፍራንክፈርት እና ኑርምበርግ ይሰብኩ ዘንድ አንጓዛቸው። እርግጥ፣ ዘመቻቸው ስፊ ሲሆን፣ የኑርምበርግ



(Nuremberg) ጉባኤ ግን እነዚህን መሰል እንቅስቃሴ የሚያራምዱት ሁሉ እየተያዙ ይቃጠሉ ዘንድ አወጀ።

እነዚህን ሰዎች፣ «ክርስቲያኖች» ወይም «ወንድሞች» ብሎ መጥራትን ያልፈለገችው የሮማ ካቶሊክ በዘመኑ እንቅስቃሴውን በኅብረት በማራመድ ልዩ ባደረገው በፒተር ዋልዶ (Peter Waldo) ስም በመጥራት ዋልዴንሳውያን (Waldenses) ትላቸው ጀመር። በትይዩም፣ በከተሙበት በአልፕስ ሸለቆ ስምም ቫለኖች (Vallenses) እየተባሉም በፍርርቅ ስም ይጠሩ ጀመር።

ፒተር ዋልዶ ጉዞውን በመቀጠል የደረሰበት ቦሂሚያ (Bohemia) በ1217 ዓ.ም ይሞትባት ዘንድ የተዘጋጀች ከተማ ሆነች። እርሱ ከመሞቱ በፊት ግን ለሚ ጆሮዎችን በማግኘት ስለ ክርስቶስ እና ስለ ቃሉ ሰበከ፣ አስተማረም፣ በዚህም ተደማጭነትን አግኝቶ ፍሬ በዛለት።

ከሞቱም በኋላ «ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ»ን ዋልዴንሳውያን ተግባራዊ በማድረግ በየአገሩ ተመሙ። እነ ሁስ እና ሌሎችም ተከታትለው በመምጣት ለመሥዋዕትነት ራሳቸውን ሰጡ። ርእሳነ ሊቃነ ጳጳሳት ኢኖሰንት ሣልሳዊ (Innocent III) በ1209 ዓ.ም የመስቀል ጦርነትን ሲያውጅ፣ በእወጃቸው ካልተመቿቸው ለሙ-ጥር ሰዎች መካከል ቀዳሚው የአሲሲ ፍራንሲስ (Francis of Assisi, 1182-1226 ) ነበር።

በ27 ዓመት ዕድሜው ላይ ጦርነቱ በቱርክ ሙስሊሞች ላይ እንዲከፈት ሲወሰን፣ ፍራንሲስ ኢየሱስ በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 10 ላይ የተናገረውን ትምህርት ያሰተነትን ነበር። ይኸው ክፍል በኢኖሰንት ሣልሳዊ አጽንኦት የሰጠው፣ «በምድር ላይ ሰላምን ለማምጣት የመጣሁ አይምሰላችሁ፤ ሰይፍን እንጂ ሰላምን ለማምጣት አልመጣሁም። ሰውን ከአባቱ፣ ሴት ልጅንም ከእናትዋ፣ ምራትንም ከአማትዋ እለያይ ዘንድ መጥቻለሁና» (ቍጥር 34-35) የሚለውን አስፍቶ ለጦርነቱ መውጣት የተቀደሰ ተልዕኮ መሆኑን ሲያበስር፤ ፍራንሲስ ግን በቁጥር 24-25 ላይ ቆሞ ነበር፡- «ደቀ መዝሙር ከመምህሩ፣ ባሪያም ከጌታው አይበልጥም። ደቀ መዝሙር እንደ መምህሩ፣ ባሪያም እንደ ጌታው

ከ12ኛው ክፍለ ዘመን መዝጊያ በፊት የነበሩ ዋልዴንሳውያን በቋንቋቸው ቅዱሳት መጽሐፍን በመተርጎም መጠቀም ስለ ጀመሩ፣ ብዙዎች ለወንጌል እጃቸውን ሰጥተው ነበር:: በዚህ ወቅት መጽሐፍ ቅዱሳቸውን ባለመስጠት ውሳኔያቸው ስለሚሞቱት ሰዎች ዳኛው መግለጫ ሲሰጥ፣ «በፍጹም ለሳም ውስጥ ሆነው ሞትን ለመሞት የሚናፍቁ ሰዎች ናቸው» ብሎላቸዋል::

ለ) በ1192 ዓ.ም የአራጎኑ ንጉሥ አልፎንሶ (King Alfonso of Aragon) «የዋልዴንሳውያንን ፈለግ አስተላሰሁ የሚሉ በፈረንሳይ፣ በኢጣሊያና፣ ኦስትሪያ የሚኖሩ መናፍቃን ሁሉ እንደ መሪዎቻቸው ከቅጣት አይተርፉም» ብሎ አወጀ::

ሐ) የ1212 ዓ.ም በዶምኒካን 500 ዋልዴንሳውያን ተይዘው ታሰሩ፣ ከእርሱም መካከል ቀሳውስት፣ ሀብታሞች፣ ድሆች፣ ወንዶች፣ ሴቶች ነበሩባቸው፣ በክፉል መያዛቸው ተገቢ አለመሆኑን ሲያስረዱ፣ «ቢጤዎቻችን በስዊዘርላንድ፣ በኢጣሊያ፣ በጀርመን፣ በቦሂሚያ እና በሌሎች አገራት ሁሉ አሉ፣ እምነታችን በእኛ ዘንድ የተጀመረ ሳይሆን አገራትን የሸፈነ ስለሆነ ልቀቁን» ብለው ጠይቀው ነበር:: ከሳሾቻቸው ግን ሳያዳምጡዋቸው 12 ቀሳውስትና 23 ሴቶችን በእሳት በማንደድ «እነርሱን ያየ ይቀጣ» አሉባቸው::

መ) የ1263 ዓ.ም ርእሳነ ሊቃነ ጳጳሳት ጎርጎሪዎስ 9ኛ፣ «መልካቸው፣ ዘራቸው፣ ዕድሜያቸው እና አገራቸው የተለያየ ሆኖ ቢገኝም፣ እምነታቸው ግን አንድ ሆኖ የተገኙ መናፍቃን ሁሉ ባሉበት ይጥፉ» በማለት የስደትና የግድያን አዋጅ አወጣ::

እነዚህን የመሰሉ አዋጆች፣ የሮማ ካቶሊክ ያወጣችባቸው የእነዚህ ሰዎች መሠረታዊ ትምህርት ምን ነበር? የዚህን ምላሽ በነጥቦች መደርደር ተገቢ ነው::

1. ከቅዱሳን መጻሕፍት ሌላ ተጨማሪ የእምነት መግለጫን እና ሌሎች ድርሳናትን አይቀበሉም::
2. በወንጌላት ውስጥ የተቀመጡት የኢየሱስ ንግግሮችና ትምህርቶች በሌሎች የቅዱሳን መጻሕፍት አጋዥነት ሳይብራሩ በኑሮአችን ተግባራዊ መሆን አለባቸው በማለት ለኢየሱስ ገለጻዎች ከፍተኛ ስፍራን ይሰጣሉ::



3. ክርስቶስን መስሎ መኖር የክርስቲያኖች ብቸኛ መለኪያ ወይም መለያ መሆን አለበት፣ ከዚህ ውጭ የሆነ አኗኗር ክርስቲያን ሊያሰኝ አይችልም::
4. ቅዱሳት መጻሕፍትን መረዳት እና የዳግም መወለድ ምስክርነት በውስጣችን ከሚመሰክርልን ከመንፈስ ቅዱስ የተነሣ ይረጋገጣል::
5. የተራራው ስብከት ለእግዚአብሔር መንግሥት መሠረት መንሥኤ እና ለቤተ ክርስቲያን አኗኗር መግለጫ ነው፣ ከዚህም የተነሣ የእግዚአብሔር ልጆች ሊኖሩበት ይገባል::
6. ያሳደዱንን በመበቀል፣ በመጥላትና በመዋጋት ውጤታማ እንሆንም፣ በትዕግሥት ግን፣ እስካለንበት ድረስ በመሄድ ሊያጠቃን የሚመጣውን ለመከላከል ነቅቶና ታጥቆ መጠበቅ ተገቢ ነው::
7. ከሮማ ካቶሊክ ጋር ኅብረት ያላቸውን ስመ-ጥር አስተማሪዎችን ሥራዎች ለመመልከት አይፈቅዱም:: ከዚህም የተነሣ፣ የአምብሮስ፣ አውግስቲንን፣ የዮሐንስ አፈወርቅን (Chrysostom) የክሌርቮውን በርናርድ ሥራዎችን አያነብቡም:: አምልኮተ ሥርዓታቸው ቀልጣፋና ቀላል ነበር::
8. የጌታን ራት በመታሰቢያነት፣ ጥምቀትንም አምኖ የተጠመቀ እንጂ፣ በሥጋ ተወልዶ የተጠመቀ ይድናል አይሉም::
9. ለወንጌል ስርጭት ሁለት ሁለት ሆነው መውጣትን እንደ ደንብ ይከተላሉ፣ ልምድን ለማግኘት ትንሹን ከትልቁ፣ አዲሱን ከከረመው፣ የተማረውን ካልተማረው፣ አቀናጅተው የማስኬድ ልማድ ነበራቸው::
10. መንፈሳዊ ሕይወት ሊያድግ የሚችለው በቅንነት፣ በየዕለቱ ከሚነበበው ቅዱሳን መጻሕፍት ነው:: ከዚህም የተነሣ፣ ይህን ዕለት ዕለት ማድረግ ተገቢ መሆኑን ያምናሉ::

***

የ1380 ዓ.ም ርእሳነ ሊቃነ ጳጳሳት ክሌመንት 7ኛ (Pope Clement VII) መልእክተኛ ወደ አሉበት ሁሉ በመላክ ለምክክር ፈለጋቸው፣ ምክክሩ ግን መናፍቃኑን ለይቶ መሪዎቹን ለማውጣት

ስለ ነበር፣ በተከታታይ ባሉት 13 ዓመቶች ውስጥ 230 መሪ አማኞች ተቃጠሉ፣ ንብረታቸውም ተወረሰ። ስደቱም እስከ 15ኛው ክፍል ዘመን ድረስ ዘለቀ። *(The Pillgrim Church*, p.120-2)

# ምዕራፍ ሃያ ዘጠኝ

## ኢትዮጵያ፣ ክርስትናና መካከለኛው የቤተ ክርስቲያን ታሪክ

የሰው ልጅ ጥንተ አመጣጥን የሚያጠኑ የሥነ ሰው አጥኚዎችና የሥነ ቁፋሮ ጠበብቶች በሚያቀርቡት የጥናት ውጤት ኢትዮጵያ እና ዙሪያዋ ያሉ አገራት ትኩረት የተገባቸው ሆነዋል።

ኢትዮጵያ፣ በተለይም በሀዳር የተገኘችው የ3.2 ሚሊዮን ዕድሜ ያላት «ሉሲ» ወይም «ድንቅነሽ» በመባል የምትታወቀው የሥነ ቁፋሮ ውጤት፣ አገሪቱን በሚገባ ለማወቅ ብዙዎችን አነሣሥታለች። በቅርቡ የቻርለስ ዳርዊንን ተፈታታኝ ተግዳሮት በመፈታተን ላይ ያለችው፣«ሰላም» በመባል የተጠራች የሴት ልጅ አጽም ሉሲን በ150.000 ዓመት ብልጫ ያላት በአፋር ስምጥ ሸለቆ በቅርቡ ተገኝታለች። ይህችም የሰውን ታሪክንና የኢትዮጵያን ገጽታ በተለየ መልክ ለማሳየት የምታስችል ግኝት ሆኗለች። «ሰላም» በተክለ ሰውነቷ ዛሬ ላይ ካለው የሰው ልጅ ቁመና ጋር ተመሳሳይ ሆና መገኘቷ የዳርዊንን «የዝግመተ ለውጥ» ምንነትን አጠያያቂ በማድረግ ለኢትዮጵያ ኩራት ሆናለች።

***

የክርስቲያናዊ ታሪክ በሚዘከርበት ጊዜ ሁሉ መነሻ ነጥቦች በመረጃዎች መደገፋቸው፣ እንዲሁም ከመጽሐፍ ቅዱስ ገለጻ ጋር መጣጣምን ማየት ተፈላጊ በመሆኑ፣ ኢትዮጵያን አስመልክቶ የቅድመ-ክርስትና መገለጫዋ ብዙዎች እንደሚስማሙበት ዘፍጥረት 10:1-29 ይሆናል። ይህ ንባብ በቅድሚያ ወደ ኢትዮጵያ የገቡት የነገደ ኩሽ ዝርያዎች ሊሆኑ እንደሚችሉ ይጠቁመናል። እነዚህ



ዝርያዎች አፍሪካን በማካለል ይኖሩ ነበር፣ የያፌት ዝርያዎችም አውሮፓን ያካለሉ መሆኑን ይጠቁማል።

በተመሳሳይ ጊዜም፣ በእስያ በስፋት እንዲሁም በደቡብ ዐረቢያና በአካባቢው ከሴም ነገድ ውስጥ የተወሰኑት ከትመው ነበር። እነዚህ ሴማውያን (ሳባውያን) ወደ ሰሜኑ ኢትዮጵያ ወይናደጋ እና ደጋማ አካባቢ በመምጣት ለመስፈር ሙከራ አድርገዋል። የኩሽ ሕዝብ የደረጀ አቋም ግን ለበርካታ ምእተ ዓመታት ሳያስጠጋቸው ቀርቷል። በጊዜ ብዛት ግን የሴም (የሳባ) ነገድ አካባቢውን በመቆጣጠር ራሳቸውን «አግዐዝያን-ነፃ አውጪዎች» በማለት መሥርተዋል።

የአክሱም መንግሥትን ኋላ ላይ ለመመሥረት የበቃውና ቋንቋው ሳባውያን በመባል በታሪክ የተጠቀሰው ይህ ሕዝብ ነው። በአሁኑ ወቅት በትግራይ ክልል ሳባ፣ እንሳባ የሚባሉ ቦታዎች መገኘት ለዚህ ጥናት ፍንጭ ነው። በተያያዥ ኢትዮጵያ በጥንት የግብፃውያን ቋንቋ ፑንት፣ ቶ፣ ኔቶር፣ ኩሽ እየተባለች ትጠራ እንደ ነበር አባ ጎርጎሪዎስ ያዘጋጁት መጽሐፍ ያብራራል።

ፑንት (ፉንጥ) በብሉይ ኪዳን ዘፍጥረት 10:6 ላይ ካለው ፋጥ ጋር ይቀራረባል፤ ቶ፣ ኔቶር በትርጉሙ «አገረ እግዚአብሔር» ማለት ነው፣ ሙሴ ይህችኑ አገር ኩሽ በማለት ጠርቷል። የዚህ መንሥኤው የግብዕ ቋንቋን ማወቁ ነበር። ኢትዮጵያ ኩሽ ለመባል የበቃችበትም ዐቢይ ምክንያት የመጀመሪያዎቹ የካም ዘሮች የሰፈሩበት ስፍራ (አገር) መሆኗ ነው። በዚህች አገር ከ3,600 ዓመት ከጌታ ቀድሞ በነበረበት ጊዜ የነገደ ሴም ወገኖች በባብ አልመንዱብ («የመከራ በር» ማለት ነው) በኩል ገብተው የከተሙ መሆናቸው ይታወቃል።

እነዚህ ወገኖች ከኩሽ ዘሮች ጋር እየተጋቡ መስፋታቸውና አገሪቱንም ምድረ አግዐዚያን በማለት «ነጻነት ያላቸው ሰዎች መኖሪያ» በማለት መጥራታቸውንና በመጨረሻም «ኢትዮጵያ» የሚል ስም መያዟን ቀደም ብለን ገልጸናል።

አንዳንዶች እንደሚሉት፣ ኢትዮጵያ የሚለው ቃል የተወሰደው «ኤቶስ» የጠቆረ፣ «አፕ-ሲስ» ገጽ አርአያ ማለት ሲሆን፣ ቅልቅሉ

«ኤቶኦ ፒያ» በመሆን፣ «የጠቆረ የበረሃ ሻንቅላ» የሚል ፍች ይሰጣል።

መጻሕፍተ ብሉያትን ከዕብራይስጥ ወደ ዕርዕ የመለሱት ሰባው ሊቃውንት ሙሴ ኩሽ እያለ በዕብራይስጡ ብሉይ ኪዳን የጻፈውን «ኢትዮጵያ» በሚል ቃል ለውጠውታል።

የግሪኮች ባለ ቅኔ ሆሜር፣ «የኢትዮጵያ ሕዝብ በጉልበት ኃያል፣ በውበት የተደነቁና ጭምቶች ስለሆኑ፣ ከግሪክ 12 አማልክት አንዱ ዜውስ ከእነርሱ ጋር ለመብላት ወደ ውቅያኖስ ወረደ» ብሎ ጽፏል።

490 ዓመት ከጌታ ልደት በፊት የነበረው የታሪክ አባት ሔሮዶቶስ፣ «ኢትዮጵያውያን በውበት፣ በቁመትና በኃይል ከሰዎች ሁሉ የሚበልጡ» ናቸው በማለት በሔሮዶቶስ 3ኛ መጽሐፍ ምዕራፍ 20 ላይ አንሥቷል።

መጽሐፍ ቅዱስም ኢትዮጵያን ከተናጠልና ከግብጽ ጋር በማያያዝ በተደጋጋሚ ገልጧል (ዘፍጥ. 2:13፤ መዝ. 66:3፤ ኢሳ. 20:3፤ ሕዝ. 29:10፤ ኢሳ. 18:1፤ ኢዩ. 28:19)። በዚህ ስም የምትጠራው ሀገር ስፊና ከአሁኗ ኢትዮጵያ በሁሉ ነገር የተበረታች ስትሆን፣ ይህቺን አገር አካታ ያለች የሰፊና የኃያል ሕዝብ መጠሪያ እንደ ነበረች መገመት ዝግጅቱን አዳባሪ ያደርገዋል።

በተይዩ፣ የነገደ እስራኤል ወደ ኢትዮጵያ መምጣት ታሪክን በተመለከተ 1ኛ ነገሥት 10:1-13 መነሻ በመሆን ይጠራል። የሳባ ንግሥት የነበረችው ሰሎሞንን ለመጎብኘት በሄደች ጊዜ፣ በጉብኝቷ ይዛ የሄደችው ስጦታ የተገኘበት፣ እንዲሁም «በአፈ ታሪክነት» እንደ ተጻፈው ስንጉሡ የፀነሰችው ልጅ ካደገ በኋላ ወደ አባቱ በመሄድ መተዋወቁና ሲመለስ ብዙ አይሁዶችን ይዞ ወደ ኢትዮጵያ መግባቱ፣ ዛሬ ላይ ላሉት «ፈላሻዎች» ወይም «እስራኤል-ተኮር የሆነ የቤት መቅደስ ሥርዓት» መነሻ ሆነዋል ይባላል። ይህ በጽኑ መረጃ ያልተረጋገጠ ቢሆንም፣ ንግሥት ሳባ በማቴዎስ 12:42 ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የ«ዓዜብ ንግሥት» በማለት መጥራቱ፣ «ሳባ»ም ሆነ «ዓዜብ» የአቅጣጫ መለያ ሰፍራዎች መሆናቸውን ማረጋገጥ አስችሏል።



ከዚህ በተሻለ ግን፣ እስራኤላውያን በኢትዮጵያ መገኘታቸው መንሥኤ በብሉይ ኪዳን እስራኤል በተደጋጋሚ በባቢሎናውያን በአሶራውያን መወረር፣ እንዲሁም በምናሴ ዘመን ካህናት ወደ ግብፅ ወደ ኤሌፋንታይን መሰደድ፣ ኋላም ወደ ኢትዮጵያ የመምጣት፣ እንዲሁም በ70 ዓ.ም በሮማዊው ቲቶ ወረራ ሕዝቡ በመከረኛነት ሕይወት በማለፍ በሕይወት የተረፉት በመሰደድ ወደ ኢትዮጵያ ሳይመጡ አልቀሩም።

እንዲህም ቢሆን፣ የኢትዮጵያ የቅድመ-ክርስትና ታሪክ ከፍተኛ እስራኤላዊ ተጽዕኖ አይታይበትም፣ ለዚህ ምክንያቱ ይሁዲነት መንግሥት-አቀፍ እምነት ባለመሆኑ ሊሆን ይችላል። ይልቅስ፣ በዚያን ጊዜ የነበሩ ቅርሶች እንደሚያስረዱት፣ የጥንታዊ ነገሥታት የገንዘብና የሐውልት ምልክቶች ሁሉ የነበራቸው ቅርጽ የነገሥታቱን ጣዖት አምላኪነት የሚያመለክት እንጂ፣ የአይሁድ እምነትን እንደ ተቀበሉ አያመላክትም።

የክርስትና በኢትዮጵያ የመጀመር እንቅስቃሴን በተመለከተ በርካታ የመነሻ ነጥቦች አሉ፣ ከእነዚህ አንዱ በሐዋርያት ሥራ 8:26-38 ያለው ገለጻ ነው። ጃንደረባው የኢትዮጵያ ንግሥት ህንደኬ መልእክተኛ ነበር፤ ወደ ኢየሩሳሌም የሄደው ሊሰግድ ነበር፣ ይህም የአይሁድ እምነት በኢትዮጵያ እንደ ነበር ይጠቁማል፤ ባለሥልጣኑ ክርስቶስን አምኖ ወደ ኢትዮጵያ ከተመለሰ በኋላ ስላደረገው ነገር መጽሐፍ ቅዱስ ምንም ነገር አይልም፤ ቢኖር ግን በንግሥቲቱ ቤሪያ ያለ ሰው እስከ ሆነ ድረስ በጎ ተጽዕኖ የማሳደር አቅም ኖሮት የክርስትናን የዕድገት መነሻ ከዚያ ማድረግ ያስችል ነበር። የማኅበረ ቅዱሳን *«ቤተ ክርስቲያንና ዕውነት»* በሚለው መጽሐፍ በገጽ 93-95 እና 145-146 ላይ ግን ጃንደረባው ከ34 ዓ.ም ጀምሮ ወንጌልን መስበኩና ቤተ ክርስቲያናትን መመሥረቱን ይዘረዝራል።

ከዚህ ጃንደረባ በመቀጠል በተቀራረበ የታሪክ ዘመን የሚነሣው ሌላው ሰው ሐዋርያው ማቴዎስ ነው። ሐዋርያው የምሥራቹን ቃል ይዞ ወደ ኢትዮጵያ በመምጣት መስበኩን፣ ብዙ ተከታዮች

በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ለወንጌል ስርጭት የነበረው አቅጣጫ ቀጣይነት ቢኖረውና የተዛነፉ አስተምህሮዎችን በማስተካከል የመድረስ አደረጃጀት ቢኖር፣ ኢትዮጵያ በነፍስም በሥጋም የበርካታ ዕድገቶች ምሳሌ ልትሆን እንደምትችል *«በመከራ ውስጥ ያበበች ቤተ ክርስቲያን»* ዘገባ በገጽ 22 ላይ ጽፏል።

ከሮም ውድቀት እስከ ተሐድሶ ዘመን ድረስ ያለውን አውሮፓውያን «የጨለማው ዘመን» ብለው ይጠሩታል። ይህን ያሉበት ምክንያት፣ ቀድሞ የነበረው ሥልጣኔ በመውደሙ፣ ኋላም ቤተ ክርስቲያን የፖለቲካ አጀንዳን ማስቀደም ሥራዬ ብላ መያዟ፣ የአረማውያንና የእስልምና ጥቃት በቤተ ክርስቲያንና አገሪት ሁሉ ላይ ከመድረሱ አኳያ የሚታይ ሲሆን፣ በተለይም በግሪክና በሮም ሥልጣኔ እየደበዘዘ መኖሩ ዘመኑን የ«ጨለማ ዘመን» አስብሎታል። ይህን ጨለማ ግን ቤተ ክርስቲያን እየተከላከለች ብርሃን የሆነችባቸው የትግል ዘመናት እንደ ነበሩ ቀደም ብሎ በኢትዮጵያ የተከናወኑ ክንውኖችን ልብ ማለት ተገቢ ነው።

ተሐድሶ በአውሮፓ ከመጀመሩ ከ100 ዓመት በፊት ቀድሞ በተለይም ከ1434-68 ዓ.ም በንግሥና ላይ የነበረው ዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ በነበረበት ዘመን ከፍተኛ የወንጌል ዘመቻ በኢትዮጵያ ተነሥቶ ነበር። በጊዜው የነበረው እንቅስቃሴ «ደቂቀ እስጢፋኖስ» በመባል ይጠራል። ስለ እነዚህ ሰዎች የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንደሚገልጸው፡-

> «. . . ደቂቀ እስጢፋኖስ የሚባሉ ለእመቤታችንና ለቅዱስ መስቀል ስግደት አይገባም የሚሉ መናፍቃን ተነሥተዋል። መናፍቃኑ ንጉሡ ባሉበት ሊቃውንቱን ተከራክረው ረቷቸው፤ ከዚህ በኋላ እነደቂቀ እስጢፋኖስ ለፍርድ ቀረቡ፤ ንጉሡም ፍርዳቸውን ከምእመናን እንዲቀበሉ ወሰኑ። ምእመናን ሲጠየቁ፣ ሁሉም በሞት ቅጣት እንዲቀጡ በየነባቸው። በመጨረሻም፣ አፍንጫቸውን ተፎንነው (ተቆርጠው) ምላሳቸውን ተቆርጠው በድንጋይ ተወግረው የካቲት ሁለት ቀን ሞቱ፤ በ38ኛው ቀን በዚያ በታ ብርሀን ወርዶ ታየ፣ ስለዚህም ስፍራው ደብረ ብርሃን ተብሎ ተሰየመ።» *(<u>የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ አስተዋጽኦ</u>፣ ገጽ 69)* ተብሎ ተጽፏል።

እስጢፋኖስ በተወለደ ጊዜ የወቅቱ ንጉሥ ቀዳማዊ አፄ ዳዊት ነበሩ። በዚህ ሰው ዘመን ግማደ መስቀሉ እና ሌሎችም ሥዕሎች ከኢየሩሳሌም መጥተዋል ይባል ነበር። ከዳዊት እስከ ዘርዓ ያዕቆብ ድረስ በአሥር ዓመቶች ውስጥ ስድስት ነገሥታት ከዙፋን ላይ ተቀምጠዋል፤ ኋላ ላይ ግን ዘርዓ ያዕቆብ በምንኩስና በገዳም ከሚኖሩበት ወጥተው፣ ቆባቸውን ቀድደው ከሁለት ሚስት ልጆችን በመውለድ ሊነግሡ ቻሉ። ንጉሡ ለሃይማኖት ፍጹም ቀናተኛ በመሆናቸው የቅጣት አዋጆች በማውጣት «መናፍቅ» የሚሉትን ለመግታት ጥረት አድርገዋል። ከአዋጁ አንዱ በደቂቀ እስጢፋኖስ ተከታዮች ላይ በግንባራቸው «በአብ፣ ወልድ፣ በመንፈስ ቅዱስ» የሚል በቀኝ እጃቸው፣ «በክርስቶስ አምናለሁ፣ ዲያብሎስን ክጃለሁ» የሚል በግራ እጃቸው፣ «የተረገመውን ድስክን ክጃለሁ፤ እኔ ሰዓሰም ፈጣሪ እናት ለማርያም አገልጋይዋ ነኝ» የሚል እንዲጻፍባቸው አዝዘዋል። ይህን ያልፈጸመም በሞት እንዲቀጡ ትእዛዝ አውጥተው ነበር። (ድስክ በወቅቱ የነበረ የባዕድ አምልኮና የርኩሳን መናፍስት አሠራር ነበር።)

አፄው በገዳም በነበሩ ጊዜ ይጽፉ ስለ ነበር ራሳቸውና አጋሮቻቸው ለማርያም፣ ለመስቀልና ለሥዕል ስግደት እንደሚገባ በርካታ ድርሳናትን ደርሰዋል፤ አስተርጉመዋልም። ከድርሳናቱ ውስጥ ተዓቅቦ ምሥጢር፣ መጽሐፈ ብርሃን፣ ተአምረ ማርያም፣ ርቱዓ ሃይማኖት፣ ጠማረ ትስብእት፣ መጽሐፈ ምዕላድ፣ አርጋን ድንግል፣ ዘለፋ እስጢፋ የመሳሰሉት በዚያን ዘመን የወጡ ናቸው። በዚያን ዘመን ከወጡት ድርሳናት ጥቂቱ ይዘውት የነበረውን አጠቃላይ ጭብጥ እንደሚከተለው ማቅረብ ይቻላል። ይህም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንን የ14ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አካሄዱን፣ በተለይም በቤተ መንግሥት ዙሪያ ምን እንደሚመስል ያመለክታል፡-

ከሚገኙበት አካባቢ በመነሣት «የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች» በመባል ይታወቃሉ። ከእነርሱ ጥቂቶቹን እንዘክር፡-

የአፋር ብሔረሰብ፡- አዳል፣ ደንከል፣ ጠልጣል በሚባሉ ስሞች ይታወቃል። ሳሆኛ ቅርበት ያለውን የኩሽ ተዛማጅ ቋንቋ የሆነውን አፋርኛን ይናገራሉ፤ ጥቂቶቹ በእርሻ ሲሰማሩ፣ ዋንኛው መተዳደሪያቸው ንግድና ከብት እርባታ ነው።

ኦሮሞ፡- አብዛኛውን የአገሪቱን የቆዳ ስፋት የያዘ ብሔር ነው። ኦሮሞዎች በእርሻ፣ በከብት እርባታ፣ በዕደ ጥበብና ንግድ ይተዳደራሉ። ብሔረሰቡ በዕድሜ መሰላል እና እርከን፣ እንዲሁም በእኩልነት ላይ በተመሠረተ «ገዳ» በተባለ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ሃይማኖታዊ ሥርዓት ይተዳደራል። በአንዳንድ አካባቢዎች ኦሮሞዎች እንደየቦታቸው በተለያየ ስም ይጠራሉ፤ ጉጂ፣ ቦረና፣ አርሲ፣ ሜጫ፣ ቱለማ፣ ኢቱ፣ ከረዩ፣ ሁሞና አብቹ፣ በቾ፣ ሰላሌ በመባል ይጠራሉ።

ይህ ሕዝብ በ16ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ላይ በሙስሊሙ ኢማም አሕመድ ግራኝና እንደ ልብነ ድንግል ባሉ «ክርስቲያን» ነገሥታት መካከል ጦርነት በየጊዜው በመቀስቀሱ፣ ከ1520 ዓ.ም ጀምሮ በተደረገው ንቅናቄ የኦሮሞ ብሔር ከደቡብ ኢትዮጵያ በመነሣት በምሥራቅ፣ በመካከለኛውና በምዕራብ ኢትዮጵያ በተለያየ አቅጣጫ ተሰራጭተዋል (ጉስታቭ አሬን፣ 1978፣ ገጽ 29)። በዚህ ስርጭት ውስጥ በአንዳንድ ስፍራዎች በመዋዋጥ፣ በሌሎች ስፍራዎች ደግሞ ማንነታቸውን በመጠበቅ በገዳ ሥርዓት ሲተዳደሩ ይገኛሉ። ሰፊ ክልል ላካለለው የኦሮሞ ብሔረሰብ በ19ኛው ክፍለ ዘመን ላይ መጽሐፍ ቅዱስን በግዕዝ ፊደል በመጠቀም በኦሮምኛ ቋንቋ ተዘጋጅቶ በአገልግሎት ላይ ያለ ሲሆን፣ ከ1983 ዓ.ም ወዲህ ደግሞ በላቲን ፊደል (በቁቤ) በመጠቀም የኦሮምኛ መጽሐፍ ቅዱስ ተዘጋጅቷል።

ሶማሌዎች፡- ኦሮምኛና አፋርኛን ጥቂቶቹ ይጠቀማሉ፤ ቢሆንም ግን፣ አብዛኞቹ የኩሽ ቤተሰብ የሆነውን የሱማልኛ ቋንቋ ይናገራሉ፤ በሐረርጌ (ሐረር)፣ በባሌና በሲዳሞ ቆላማ ሜዳዎች ከብት በማርባትና በዘላንነት ይገኛሉ።



4. ደቡብ ኩሾች- እነዚህ በሲዳሞ ሕዝቦችና በኦሮሞዎች መሀል የሚኖሩና ደራሳ (ጌዴኦ)፣ ከምባታና ሃዲያ፣ አላባና ጠምባሮ፣ ክንሶ፣ ወይም ገሰብ በመባል ይታወቃሉ፤ ቋንቋቸው ከሲዳምኛ ይልቅ ወደ ኦሮምኛ ይጠጋል።

ለ. *ኦሞአዊ ሕዝብ፡-* ይህ ሕዝብ በጋሞ ጎፋ፣ በሲዳሞ፣ በኢሉባቦርና በከፋ ተሰራጭተው በኦሞ ወንዝ ሸለቆ ሲገኙ፣ በውስጣቸው ብዙ ብሔረሰቦችን አካትተዋል (ቤንዳር፣ 1976፣ ገጽ 35)። ከጥቂቶቹ፡-

ለ.1. አሪ፣ በና፣ ዲሜ፣ አመር፣ ወባመር ሁሉም አምአዊ ቋንቋ ይናገራሉ።

ለ.2. ቤንች (በቀድሞ አጠራር ጊሚራ ሲባል)፣ ሸኮ የሚባሉ ጉሣዎችን ይጨምራል፣ የሚናገሩት ኦምአዊ ቋንቋን ነው።

ለ.3. የም፣ ጃንጀሮ፣ ያንጋሮ በእርሻና በከብት እርባታ፣ በሽመና ሥራ ይተዳደራሉ። ከእነዚህ ውስጥ የየም ሕዝብ የራሱ አስተዳደር የነበረው ሲሆን፣ ለንጉሡ የፈረስ ግብር ይሰጥ እንደ ነበር ተጽፎለታል (በንጉሡ ይስሐቅ 1412-27 ዜና መዋዕል ላይ፣ በ13ኛው ክፍለ ዘመን በደቡብ ኢትዮጵያ የበላይነትን ተቀዳጅቶ የነበረው የዳሞት መንግሥት ማዕከል እንደ ነበረም ይታወቃል።)

ለ.4. ከፋ (ከፍቾ) ጉመር የሚባል ቋንቋን ይጠቀማሉ። የቋንቋው ሥርዓት ኦሞአዊ ነው፤ ኑሮአቸው ግብርናና ከብት እርባታ ነው። በ16ኛው ክፍለ ዘመን ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ የነበረው የፖርቹጋል ተወላጅ ፍራንሲስኮ አልቫሬስ በጻፈው መጽሐፍ ውስጥ ስለ ሕዝቡ በስፋት ዘርዝሯል።

ለ.5. ማጂ ወይም ዲዚ መሣሪያዎችን ከብረት፣ ጌጣ ጌጦችን ከመዳብ፣ የቤት ቁሳቁሶችን ከሸክላ ይሠራ የነበረ ሕዝብ ነው። የሁሉም ቋንቋ ኦሞአዊ ነው።

ለ.6. ኡመቴ፣ አሊጋ፣ ኮሮ፣ ባስኬቶ፣ ባሮዳ፣ ደቅ፣ ጫራ፣ ዶርዜ፣ ማሌ፣ ዘርጉላ፣ ጋነጆላ፣ ግዶች፣ ሃሩሮ፣ ኮንታ፣ ዳወሮ፣ ወላይታ፣ ዘይዳ የሚባሉ ሕዝቦች ኦሞአዊ ቋንቋን ይናገራሉ።

ሃይማኖታዊ አስተሳሰቦች ስርገው መግባታቸውን መረዳት ተችሏል።

ከ356-323 ዓ.ዓ በግብፅና በአካባቢው ባሉ አገራት ዘንድ ግሪካዊ አስተሳሰብ እንዲስፋፋ ያደረገው ታላቁ እስክንድር ነበር፤ ይህም ለውጥ በኢትዮጵያ ውስጥ ግሪካዊ የእምነት መገለጫዎች በሰሜኑ ግዛት እንዲገኙ አድርጓል።

የኢትዮጵያ መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ ሦስት ክፍላተ ዓለማትን፣ ማለትም አውሮፓን፣ እስያንና አፍሪካን በሚያገናኝ ስፍራ ላይ መገኘቱ፣ የእነዚህን ዓለማት አስተሳሰቦች ወደ ኢትዮጵያም ተሻጋሪ እንዲሆኑ አድርጓል።

የግሪክ አማልክት በኢትዮጵያ ቅድመ-ክርስትና ገጽታ ላይ ተጽዕኖ እንደ ነበራቸው የሚሰጠን መረጃ በአክሱምና በዙሪያው ባሉ የድንጋይ ላይ ጽሑፎችና ቅርጾች ላይ የዚየስ፣ ፖሲዲየን እና አሬስ የተባሉ የግሪኮች አማልክትን ስም ማግኘት ነው፣ በተለይም በአዶሊስ ወደብ በርካቶች እስከ ዛሬ ድረስ እንዳሉ ይነገራል።

በምሥራቁ ዓለምና በአፍሪካ የተለመደው የሀንዱ የአምልኮ ሥርዓትም በኢትዮጵያ እንደ ነበር በአክሱም በተገኘው ሐውልት ላይ የሚታየው የአባብ ቅርጽ በፍንጭ ሰጪነት ተመዝግቧል (ጆንሰን፣ 1970፣ ገጽ 22)። ፋርሶች «አቬስታ» በሚሉት መጽሐፋቸው የተገለጸው የዘንዶ አምልኮ ሥርዓትና በኢትዮጵያ እንደ ተካሄደ የሚነገርለት ዘንዶዊ አምልኮ መመሳሰል በጊዜው የነበረውን የግንኙነት ስፋት በአዳባሪነት ያመላክታል።

ኢዛና ቤጃዎችን አሸንፎ ክምርኮ ሲመለስ ድል ለሰጠው ለአሬስ ክብር ሐውልት ማሠራቱ፣ ከ4ኛው ክፍለ ዘመን ቀድሞ በኢትዮጵያ የግሪካውያንና የሮማውያን አስተሳሰብ መዝለቁን ያረጋግጣል።

የኩሽ ወገን የሆኑት ኦሮሞዎችና ሲዳማዎች በእምነታቸው የሚስማሙት አምላክ ሩቅና ሊደረስበት የማይችል አድርገው ስለሚያስተውሉት፣ ከዚያ ኃያል ጋር ለመገናኘት የሥልጣን ተዋረድ ባላቸው መናፍስት አማካኝነት መገናኘት



ይመርጡ እንደ ነበር የቀድሞ ታሪክ ዘግቦ መገኘቱ የኩሻውያንን ቀዳሚነት ያስተዋውቃል። መናፍስት ሰውን በዕለታዊ ኑሮው ሊጎዱ ወይም ሊጠቀሙት እንደሚችሉ በማመናቸው በአያና፣ ዛር፣ ውቃቢ፣ አቴቴ፣ የማራም አምልኮ በሚሰኙት ግንኙነትን ይመሠርቱ ነበር። ዛር አገውኛ ቃል ሲሆን፣ «የሰማይ አምላክ» ለሚለው ውክልናን እንደ ሁኔታው ይይዛል። ሰዎች ለዛር በተገዙ መጠን ኑሮአቸው ይጠበቃል፣ ዛር ሰዎች ተሰብስበው ባሉበት ሲወርድና በተለያዩ ልሳናት ሲያናግራቸው ይችላል። አቴቴ ወይም የማራም አምልኮ በሴቶች ዘንድ «የእናትነት አምላክ» ተብላ በመጠራት ትወደዳለች፤ ብዙዎች «አያና ሃዳ» በማለት ይጠሯታል፤ አገልጋዮቿ ሴቶች ስለሆኑ፣ ተገቢ ሥርዓቱን ሁሉ ያስፈጽማሉ።

ለክርስትና የመነሻ ታሪክም የንግሥት ሕንደኬ ጃንደረባ ለኢትዮጵያ የተላከ መሆኑን የሐዋርያት ሥራ ይናገራል። ከዚህ ትረካ በመነሣት፣ ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ የመጣው ከ35-40 ዓ.ም ባለው ጊዜ ነው የሚሉ ተራኪዎች አሉ። ይህ ገለጻ አይሁዶች በኢትዮጵያ እንደ ነበሩ ሊያባቁም የመቻል አቅም ሊኖረው፣ ግለሰቡን በተመለከተ ግን ክርስትናን ለማስፋፋት ስላደረገው ጥረት ምንም ፍንጭ የለም።

ፊልጶስ ያጠመቀው ጃንደረባ በኢትዮጵያ የወንጌል ሥራን መጀመሩን፣ ፍሬምናጦስ ደግሞ የቅስናንና የቤተ ክርስቲያን ሥርዓትን በማቋቋም ክርስትናን እንዳስፋፋው በመጻፍ፣ ክርስትና በኢትዮጵያ እስከ አራተኛው ክፍለ ዘመን እንደ ዘገየ የሚተርኩ ጽሑፎች መኖራቸውን ከግምት ማስገባት ተገቢ ነው የሚሉ አጥኚዎች አሉ።

ሩፊነስና ሶቅራጥስ የተባሉ የታሪክ ጸሐፊዎች፣ «ሐዋርያት ወደ ዓለም ሁሉ» ለመሄድ ሲነሡ «የት እንደሚሄዱ» ባለማወቃቸው ዕጣ ተጣጥለዋል ይላል። በዕጣውም ለማቴዎስ የኢትዮጵያ ክልል ስለ ደረሰው፣ ወደዚህ መጥቶ ቤተ ክርስቲያን መሥርቶ መሠዋቱን ይዘረዝራሉ።

ኑቢያ (ሱዳን) አክሱም ክርስትናን ከተቀበለች ከሁለት መቶ ዓመታት በኋላ እምነቱን መቀበሏ ግን የእነሶቅራጥስን ዘገባ ጥያቄ ውስጥ ይከትተዋል። በሰነዶች የተረጋገጠስት የክርስትና ጅማሮ በፍሬምናጦስ ኋላ ላይ በኢትዮጵያውያን «ከሣቴ ብርሃን» ወይም «ብርሃንን የሚያሳይ የሰላም አባት» በተባለው ሰው ወደ ቤተ መንግሥቱ በመድረስ፣ ክርስትና የኢዛና፣ ኋላም የመንግሥቱ እምነት እንደ ሆነ ማረጋገጥ ይቻላል።

በአክሱም ክርስትና ከመስፋፋቱም የተነሣ በ325 በኒቂያ የተወሰነውን «የኢየሱስን አምላክነት» በመቀበል እነርሱም አርዮስን ማውገዛቸው በታሪክ ተጽፎ ይገኛል (አአምሮ ወንድም አገኘሁና ጆአሲም፣ 1970 ዓ.ም፣ ገጽ 100)። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እስከ 1959 ዓ.ም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጳጳሳትን ትቀበል የነበረው ከግብፅ አሌክሳንድርያ ነበር።

«ዘጠኙ ቅዱሳን» በመባል የሚታወቁት ከሮማ ግዛቶች በተለይም ከሶሪያ በ480 ዓ.ም አካባቢ ወደ አክሱም የመጡት በኢትዮጵያ ክርስትና እንዲስፋፋ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል፣ ወንጌልን ሰብከዋል፣ የአትናቴዎስን ሥራዎች ተርጉመዋል፣ መጽሐፍ ቅዱስን ወደ ግዕዝ መልሰዋል፣ የኢትዮጵያን የፊደል ገበታ በማመቻቸት ግዕዝ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዲያደርግ አግዘዋል።

እነዚህ ዘጠኙ ቅዱሳን በኬልቄዶን ጉባኤ በ451 ዓ.ም ተወግዘው፣ በስደት በግብፅ አድርገው ወደ ኢትዮጵያ እንደ መጡ ይገመታል። የኬልቄዶን ጉባኤ የክርስቶስን ፍጹም ሰው መሆንና ፍጹም አምላክ መሆኑን ያበሰረ ጉባኤ ነበር። እነዚህ ሰዎች ይህን የተቃወሙ ከሆኑ፣ ዛሬ ላይ ላለው የተዋህዶ እምነት ከፍተኛ የሆነ አስተዋጽኦ በማድረግ ለወንጌላዊ እምነት እንቅፋት ሳይሆኑ አልቀሩም።

አክሱማውያን በበላይነት እስከ 12ኛው ክፍለ ዘመን በቀጠሉበት ጊዜ ለክርስትና መስፋፋት የበኩላቸውን ያደረጉ ቢሆንም፣ እነርሱን በመቋቋምና በማሸነፍ ከ1137-1270 ዓ.ም የመሩት የዛጉዌ ነገሥታት ነበሩ። እነዚህን ነገሥታት ለሰሞናዊው መንግሥት



ባይቀበላቸውም፣ እነርሱ ግን ክርስትናን በማስፋፋት እና አብያተ ክርስቲያናትን በመገንባት ጠንክረው ስለ ነበር የሕዝብን ድጋፍ አግኝተዋል፣ አንዳንዶች እንደሚሉት ከ10ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ ለ300 ዓመታትም ሳያስተዳድሩ አልቀሩም።

ከአገው ሥርወ መንግሥት ውስጥ ከ1190-1225 ዓ.ም ያስተዳደረው ላሊበላ ከንግሥ ዘመኑ በፊት አስቀድሞ ከኖረበት የኢየሩሳሌም የምነና ዘመኑ ካገኘው ልምድ በመነሣት በንግሥና ዘመኑ ከአንድ ወጥ ድንጋይ የተሠሩ አብያተ ክርስቲያናትን አስገንብቷል። የሕንፃዎቹ ጥበብ የባይዛንታይን የሕንፃ ጥበብንና የዐረቦችን (ግብፅን) አሠራር የተመረኮዘ በመሆኑ፣ ያሠራው በውጭ ባለሟሎች ሳይሆን አይቀርም (ጆንሰን፣ 1970 ዓ.ም፣ ገጽ 49)።

ከ1270 ዓ.ም በኋላ ግን የመንግሥቱን መሠረት ሰሎሞናውያን ይዘውታል። ይህንንም የደብረ ዳሞው መነኩሴ አባ የሱስ ሞአ እና የደብረ ሊባኖሱ አባ ተክለ ሃይማኖት የዛጉዌን የመጨረሻ ንጉሥ ነአኩቶ ለአብን በማግባባት ለሰለሞናዊው መሪ ለይኩኖ አምላክ እንዲሰጥ ሳያደርጉ አልቀሩም።

እስከ 13ኛው ክፍለ ዘመን ለሰባት መቶ ዓመታት በእስልምና ማየል ምክንያት ኢትዮጵያ ከውጪው ዓለም ተለይታ እንደ ነበረች ይታወቃል። ከዚህም የተነሣ፣ ሕዝቡ ከውጪው ዓለም ጋር የነበረው ግንኙነት ሁሉ በመቋረጡ፣ የአስተሳሰብና የሥልጣኔ ድሀ እንደ ሆነ ይገመታል። ለዚህም የመነሻ ነጥቦች በሕዝቡ መካከል መጽሐፍ ቅዱስ-ተኮር ያልሆኑ አፈ ታሪኮች በብዛት መስፋፋት ውጤታማነት ለሌለው አገራዊ አኗኗር ገዝፎ መገኘት ምክንያት ሆኗል።

አገሪቱን የተሻሉ የተባሉ ከቅኔ ቤት የሚወጡና በስዋስው መጻሕፍት አውቀት የበለጸጉ በመንግሥት ሥራ ላይ በጣም ተፈላጊ እየሆኑ የመጡበት ክፍለ ዘመን በመሆኑ፣ በወቅቱ ንጉሥ ዳዊት (1380-1412 ዓ.ም)፣ ንጉሥ ዘርዓ ያዕቆብ (1434-68 ዓ.ም)፣ ንጉሥ ናዖድ (1494-1508 ዓ.ም) አገሪቱን በማስተዳደር የገዳማት ትምህርት ቤቶችን ከፈቱ፣ የትውፊት ሀብቶችንም አበለጸጉ። ይህን ከማበልጸግ ከፍተኛ አስተዋጽኦ

ያደረገው ከ1314-1344 ዓ.ም ነግሦ የነበረው በተለይም ዓምደ ጽዮን የመስፋፋት ጦርነቶችን በማድረግና በዙሪያው ያሉትን ሙስሊሞች በማስገበር ወደ ለሜን፣ ደቡብና ምሥራቅ አቅጣጫ ወጣ። በዚህም ዘመቻ ይፋት፣ ሀዲያ፣ ዳውሮ፣ ባሌና አዳል የመሳሰሉትን የእስላም ግዛቶችን ይዞ ሕንፃዎችን ማስገንባትና በጣና ሐይቅ ላይ ገዳሞችን ማቋቋም ቻለ። እንዲህም ቢሆን ግን፣ የክርስትና ስርጭትን በተመለከተ በአክሱም ዙሪያ የነበሩ ከባህላዊ አምልኮ ተለይተው ስለ ወንጌል የሰሙት የአክሱም መንግሥት ክርስትናን ከተቀበለ ከ200 ዓመታት በኋላ መሆኑ፣ ወደ ዛጉዌ ነገሥታት መቀመጫ ወደ ነበረችው ወደ «ሮሃ-ላስታ» የደረሰው በ13ኛው ክፍለ ዘመን መሆኑ፣ ወደ ጎጃምና ጎንደር የደረሰው በ15ኛው እና በ16ኛው ክፍለ ዘመን መሆኑንና ከጅባት ጀምሮ በሃዲያ በማለፍ እስከ ሰሜናዊ የባሌ ድንበር ድረስ ስለ ክርስትና እምነት የሰሙት ከ16ኛው ክፍለ ዘመን በኋላ መሆኑ፣ ዓምደ ጽዮን በ14ኛው ክፍለ ዘመን ባሌን ሲያስገብር ክርስትናን እንዳላሰበበት ይጠቁማል። በወለጋ፣ በከፋ፣ በኢሉባቦር፣ በጋሞ ጎፋ፣ በሲዳሞና በባሌ አካባቢ የክርስትና እምነትን የተረዱት ከ19ኛው ክፍለ ዘመን በኋላ ነበር። በ20ኛው ክፍለ ዘመን አፄ ምኒልክ የመስፋፋት ጦርነት ሲያደርጉ፣ አብረዋቸው የኦርቶዶክስ ቀሳውስትንና ደብተራዎችን ይዘው ይዘምቱ ስለ ነበር፣ ለወንጌል መስማት በመጠኑ ምክንያት እንደ ሆኑ ይገመታል።

ለክርስትና መስፋፋት የመዘግየት መንሥኤ ከሆኑት አንዱና ዋንኛው ግን ከጦሩ ጋር የሚዘምቱ ካህናት የወረሩትን ሕዝብ ስለ ክርስትና ሳያስተምሩት ተልዕኮአቸው አብሮ ዘምቶ ለነበረው ወታደርና በዚያ የነበሩ ተባራሪ ጥቂት ክርስቲያኖችን ብቻ በማገልገል ላይ ያተኮረ ስለ ነበር፣ ምንም ዓይነት ዕድገት አልተመዘገበም። ለዕድገቱ መጫጨት ሌላው ተጠሪ በመካከለኛው ክፍለ ዘመን የነበረው የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ውስጣዊ አደረጃጀት ብቃት የጎደለው መሆን ነበር። ማዕከላዊነትን በጠበቀ ሁኔታ ተያያዥነት ባለመኖሩ፣ ብዙዎች ቤተ ክርስቲያናት በተመሠረቱበት ለበርካታ መቶ ዓመታት ተትተዋል።



በክርስትና እምነትና ትምህርቶች ዙሪያ የሚነሡ አለመግባባቶችም ሌላኛው የመዳከሚያ አቅጣጫ ሲሆኑ፣ ጳጳሳት ከአሌክሳንድርያ በመምጣት የፈየዱት ሥራ ከሃይማኖታዊ ገጽታው በበለጠ ፖለቲካዊ አጀንዳው መብለጡ፣ እንዲሁም ቤተ ክርስቲያኒቱ የክርስትና ደሐራዋን አዲስ ኪዳናዊ መሠረት ላይ ሳይሆን፣ ሥርዓተ አምልኮው አሪታዊ ገጽታን መያዙ፣ አጠቃላይ ዕድገቱን ገትቶ እንደ ያዘው ተመሪማሪዎቹ ያመለክታሉ።

እንዲህም ቢሆን ግን፣ በተለይም በ14ኛው ክፍለ ዘመን ላይ የተገኙት የደቂቀ እስጢፋኖስ እንቅስቃሴዎች በሮም ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ላይ እነ ማርቲን ሉተር የተሐድሶ እርምጃ ከመውሰዳቸው ከ150 ዓመት ቀድሞ በአገራችን መካሄዱና መሰል እንቅስቃሴዎች መኖራቸው በጎ አስተዋጽኦ ውስጥ ያስቆጥራቸዋል። የመካከለኛው የቤተ ክርስቲያን ታሪክም በኢትዮጵያ ውስጥ በአብዛኛው በፈዘዘ መልኩ በጥቂቱ በስሙ-ጥር አቅጣጫው ተነሽ ታሪክን መዝግቦ ማለፉን ልብ ማለት የነገን አቅጣጫ በአግባቡ እንድናይ ያደርገናል።